# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 097 ታኅሣሥ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# ባይደን አፍሪካውያንን የዲጅታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርግ አዲስ እቅድ ይፋ አደረጉ

ጀማል ታመነ



ዋሽንግተን፡- የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በአፍሪካ ዜጎች የዲጅታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የ350 ሚሊዮን ዶላር እቅድ ይፋ አደረጉ። የአሜሪካ አፍሪካ መሪዎች የቢዝነስ ፎረም በዋሽንግተን ዲሲ ትናንት ተካሂዷል።

የአሜሪካ አፍሪካ መሪዎች ጉባኤ በሁለተኛ ቀን ውሎው በቢዝነስ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መክሯል በመድረኩ የተገኙት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ባደረጉት ንግግር፤ አገራቸው በአፍሪካ አህጉር የኢኮኖሚ ለውጥ እንዲመጣ በቀጣይ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በእቅድ ይዛለች ብለዋል።

ከዚህ ቀደም አሜሪካ በአፍሪካ አህጉር በመሰረተ ልማትና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ያላትን ተሳትፎ የጠቀሱት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፤ ይህ ጉባኤ በቀጣይ አሜሪካና አፍሪካ ያላቸውን ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚረዳ እንደሆነም አንስተዋል።

በመድረኩ ፕሬዚዳንት ባይደን በአፍሪካ ይተገበራል ያሉትን አዲስ እቅድ ይፋ አድርገዋል። ይህ እቅድ የዲጅታል ሽግግር ከአፍሪካ ጋር የተሰናሰነ ሲሆን 350 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የሚደረግበት ይሆናል ብለዋል።

እቅዱ በዋናነት አፍሪካውያን በዲጅታል ኢኮኖሚ ውስጥ እንዲሳተፉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑንም ተናግረዋል።

በዚህ ሂደት ማይክሮሶፍትና ቪያሳት የተሰኙ የኢንተርኔት አቅራቢ ድርጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አምስት ሚሊዮን አፍሪካውያን የኢንተርኔት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላልም ብለዋል።

ጆ ባይደን የሚመሩት አስተዳደር ባለፉት ሁለት ዓመታት ከመጣ ወዲህ በአፍሪካ ከሚገኙ በርካታ ሀገራት ጋር ያለው የኢኮኖሚ ትብብር ማደጉን አንስተዋል። ይህ

ባይደን አፍሪካውያንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


# ታሪፍ ባልወጣለት መንገድ ምክንያት ለእንግልትና ለአላስፈላጊ ወጪ ተዳርገናል

- የሚዛን ከተማ ነዋሪዎች

# አዲስ ታሪፍ በማውጣት ችግሩን ለመቅረፍ እየሠራሁ ነው

- የሱሉልታ ከተማ ትራንስፖርት ጽህፈት ቤት

ታደሰ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ከአዲሱ ገበያ ፍተሻ የሚወስደው መንገድ ጥገና ላይ በመሆኑ እና ለተለዋጭ መንገዱ ታሪፍ ባለመውጣቱ ለእንግልትና ለአላስፈላጊ ወጪ መዳረጋቸውን የሚዛን ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ፡፡

በአዲሱ ገበያ፣ ድል በር፣ ፍተሻ የሚወስደው መንገድ ጥገና ላይ በመሆኑ ምክንያት በአዲሱ ገበያ፣ ሽሮ ሜዳ፣ እንጦጦ ፍተሻ የሚወስደውን ተለዋጭ አማራጭ መንገድ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ እና ለተለዋጭ መንገዱ

ታሪፍ ባልወጣለት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ያላትን ተደማጭነትና ታሪካዊ ኃላፊነት የሚመጥን ሥራ እየሰራች ነው

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ- የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ የውስጥ ችግሮቿን በመፍታት በዓለም አቀፍ መድረኮች ያላትን ተደማጭነትና ታሪካዊ ኃላፊነት የሚመጥን ሥራ እየሰራች መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም ለጋዜጠኞች በሰጡት ሳምንታዊ መግለጫ እንደገለጹት፣ በአሜሪካ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ኢትዮጵያ የውስጥ ችግሮቿን ፈታ በዓለም አቀፍ መድረኮች ያላትን ተደማጭነትና ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣት እየሰራች ነው፡፡ በጉባኤው ላይ መንግሥት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነትና እየተወሰዱ ያሉ አበረታችና ጠቃሚ የሆኑ ርምጃዎችን ለማስረዳት እድል የፈጠረ የዲፕሎማሲ መድረክ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ቃል አቀባዩ ማብራሪያ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር

ኢትዮጵያ በዓለም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አምባሳደር መለስ አለም



# “በዲፕሎማሲ ከተመዘገቡት ድሎች ባሻገር ለነበሩ ክፍተቶችም ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል”

- ዲማ ነገዎ (ዶ/ር)

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- አገሪቱ በዲፕሎማሲ ዘርፍ ያስመዘገበችው ስኬቶችን ለማጎልበት እና የነበሩ ክፍተቶችን ለማረም ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰላምና የውጭ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዲማ ነገዎ (ዶክተር) አመለከቱ፡፡

ዶክተር ዲማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት በፈተና ውስጥ የተከናወኑ አመርቂ ተግባራት ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአገር ላይ ሲወርድ የነበረው ፈርጀ ብዙ ጫና በተገቢው ሲጤን የአገሪቱ ዲፕሎማሲ ሥራ ላይ እርማት እንደሚያስፈልግ ቁልፍ አመላካች ነው፡፡

የኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ በተከታታይ ለ13 ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ሲቀርብ በቀላል የሚተውና የሚረሳ ጉዳይ እንዳልሆነ የጠቆሙት

“በዲፕሎማሲ ከተመዘገቡት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ክላሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነጻነት አዋጆችን በአግባቡ መተግበር እንዳልተቻለ ተጠቆመ

ገጽ 3

# በሰብል ምርታማነት ላይ እየተመዘገበ ያለውን ስኬት በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ዘርፉ ለማስቀጠል እየተሰራ ነው

\- ግብርና ሚኒስቴር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**





አዲስ አበባ፡- በሰብል ምርታማነት እየተመዘገበ ያለውን ስኬት በእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ለማስቀጠል በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ እንደገለጹት ኢትዮጵያ በርካታ የእንስሳት ሀብት ያላት አገር ብትሆንም ከዘርፉ በሚገባት ልክ ሳትጠቀም ቆይታለች፡፡ በመሆኑም መንግሥት በተለይ በስንዴ ልማት ላይ በአጭር ጊዜ ያስመዘገበውን ስኬት በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ላይ ለማስቀጠል እየሰራ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ፕሮጀክት አማካኝነት አነስተኛ ገቢ ያላቸው አርሶ አደሮችን፣ ሥራ አጥ ወጣቶችንና ሴቶችን በማደራጀት ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ጠቅሰዋል።

ፕሮጀክቱ በአገር አቀፍ ደረጃ እየተተገበረ ሲሆን፤ በዚህም በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ሥራ ፈጠራ እና የተሻሻሉ የወተት ላም ዝርያዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን ለኢዜአ ገልጸዋል።

በተጨማሪም በቅርቡ በተጀመረው የሌማት ትሩፋት መርሃ-ግብር የወተት፣ የሥጋ ፣ የዶሮና እንቁላል፣ የማርና የዓሳ ምርታማነትን በማሳደግ የተመጣጠነ የሥነ-ምግብ ሥርዓት እንዲፈጠር እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል።

የአገር ውስጥ የላም ዝርያዎች በሰው ሰራሽ ዘዴ ከውጭ ከመጡ ዝርያዎች ጋር በማዳቀል በቀን እስከ 15 ሊትር ወተት እንዲሰጡ ማድረግ መቻሉንም ገልጸዋል።

በአገር ውስጥና በተሻሻሉ የላም ዝርያዎች መካከል ያለውን የወተት ምርት ልዩነት ለማጥበብም በሰው ሰራሽ የማዳቀል ሥርዓት የወተት ላሞችን የማባዛት ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ አንስተዋል።

ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ በማስገባትና በሰው ሰራሽ የማዳቀል ሥርዓት ሴት ጥጆችን መውለድ የሚያስችል የማዳቀል ሥራ እየተከናወነ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በሚኒስቴሩ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ፕሮጀክት ብሔራዊ አስተባባሪ ዶክተር ቶማስ ቸርነት፤ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ከ10 ሺህ በላይ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ሥራ አጥ ወጣቶች፣ ሴቶችና አነስተኛ ገቢ ያላቸው አርሶ አደሮችን በማደራጀት በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሥራ እንዲሰማሩ መደረጉን ገልጸዋል።

አርሶ አደሮቹ ከራሳቸው አልፎ ለየአካባቢያቸው ነዋሪዎችም የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እያደረጉ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የወተት ምርታማነትን ለማሳደግም የተሻሻለ ዝርያ ያላቸውን ላሞች በማባዛት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እየተደረገ እንደሚገኝ አንስተዋል።

ፕሮጀክቱ በአገር አቀፍ ደረጃ እያከናወነ ባለው የልማት ሥራ በአጠቃላይ ከ120 ሺህ በላይ ዜጎችን በቀጥታ፤ ሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎችን ደግሞ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል። የወተት ላሞችን ተደራሽ ለማድረግ የተጀመረው ሥራም በቀጣይ ተጠናክሮ ይቀጥላል ተብሏል፡፡



# በቀን እስከ አንድ ሚሊዮን ዳቦ ማምረት የሚችለው ከረዩ የዳቦ ፋብሪካ ተመረቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በሂማ ማኑፋክቸሪግ ኩባንያ ሙሉ ወጪ እና በከተማ አስተዳደሩ የቦታ አቅርቦት የተገነባው ከረዩ የዳቦ ማምረቻና ማከፋፈያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተገኙበት ትናንት ተመረቀ፡፡

ከ140 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ማምረቻና ማከፋፈያ ተመረቀ፡፡ በቀን ከ 150 ሺህ እስከ 200 ሺህ ዳቦ በማምረት ላይ ሲሆን በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ሲገባ በቀን 1 ሚሊዮን ዳቦ እንደሚያመርት ተጠቁሟል፡፡

ለዳቦ ማምረቻ እና ማከፋፈያው መንግሥት ዱቄት የሚያቀርብ ሲሆን የንግድ ቢሮ በሚያወጣው ቅናሽ የዳቦ መሸጫ ተመን እንደሚያከፋፍልም ተገልጿል፡፡

ከንቲባ አዳነች «በሰው ተኮር የልማት ስራዎች የተሰራ የዳቦ ፋብሪካ አስመርቀናል» ብለዋል፡፡

በከተማው የሰው ተኮር የልማት ስራዎች ዙርያ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለተለያዩ በጎ ፍቃደኞች በቀረበው ግብዣ መሰረት በቀን እስከ አንድ ሚሊዮን ዳቦ ማምረት የሚችል የዳቦ ፋብሪካ ከበጎ ፍቃደኛ የግል ባለሀብት ሂማ ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ጋር በትብብር ተገንብቶ ለምረቃ መብቃቱን ተናግረዋል፡፡

ፋብሪካው በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ዳቦ የሚያቀርብ፣ ምንም ገቢ ለሌላቸው በነፃ የሚያቀርብ፣ ለብዙ የአካባቢው ወጣቶች የስራ እድል የፈጠረ እና እርስ በእርስ የመረዳዳትና የመተሳሰብ ባህላችንን የሚያሳድግ ጭምር ነው ብለዋል ከንቲባ አዳነች።

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ ወ/ሮ መህቡባ ሰይድ የሂማ ማኑፋክቸሪንግ ፒ ኤል ሲ ስራ አስኪያጅ ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ላሳዩት ሀገር ወዳድነትና በጎነት ልባዊ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ሰርተን የምንለወጥባት፤ ነግደን የምናተርፍባት ከተማችን አዲስ አበባን ከራሳችን አልፎ ሌሎችንም ወገኖቻችንን የምናስታውስበት ማህበራዊ ሃላፊነታችንን በመወጣት በኩል ተምሳሌታዊ የሚሆን ተግባር ነው፡፡

በከተማው አብሮነትና ፍቅር፣ ተሳስቦ የመኖር እሴት በመጠበቅ በጀመርነው የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴ የግል ሴክተሩ፣ ግለሰቦችና ድርጅቶች ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ከንቲባዋ፤ የከተማዋን ነዋሪዎች ገበታ ሙሉ እና የተመጣጠነ እንዲሁም ለጎረቤትና ለአካባቢ የሚተርፍ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ግሎባል አልያንስ በአረንጓዴ ልማትና በሰብዓዊ ድጋፎች ዙሪያ ሥራዎቹን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- አህጉር አቀፍ ኢትዮጵያውያን ሕብረት/ግሎባል አልያንስ/፣ ከሲቪል ማህበረሰብና ሌሎች የልማት ማሕበራት ጋር በመተባበር መልሶ መገንባት፣ በአረንጓዴ ልማትና በሰብዓዊ ድጋፎች ዙሪያ የሚሰራቸውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ፡፡

የግሎባል አልያንስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ በትሩ ገብረ እግዚአብሔር እንደገለጹት፣ በዘላቂ ልማት ጉዳዮች ላይ የጋራ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በመልካም አስተዳደር ችግር እና በሰብአዊ መብት አጠባበቅ ዙርያ አጠናክሮ የሚሰሩት ይሆናል፡፡

ግሎባል አልያንስ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት እንዲከበርና ሰብአዊ እርዳታ ለዜጎች እንዲዳረስ ባለፉት 10 ዓመታት ግንባር ቀደም ሚናን ሲጫወት መቆየቱን ያነሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ አሁንም በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚስተዋለው የንጹሃን ዜጎች ችግር ለመግታት የኩላቸውን ሚና ለመወጣት ጥረት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በአገራችን ያሉ በርካታ የማህበረሰብ ተቋማት ከመንግሥት ጋር በመሆን ሥራ ሊሰሩ ይገባል ያሉት አቶ በትሩ፤ በንጹሃን ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ መቃወም እንደሚገባቸውና የግሎባል አልያንስ ለኢትዮጵያውያን መብት አንዱ ዓላማም ሕዝቡ ለመብቱ እንዲቆም መሆኑን አስታውሰዋል።

በቅርቡ የተመሰረተው፣ ሕብረት ለአንጓዴ ልማትና ኢትዮጵያን በጽኑ መሰረት ላይ ማቆም የሚል ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር እሸቱ በቀለ በበኩላቸው፣ የሰው ልጆች ለመኖር የሥራ እድል፣ መሬት፣ አካባቢያዊ ሁኔታ፣ የተፈጥሮ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመኑ መምጣታቸውን ገልጸዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የአካባቢ ሙቀት፣ የሰደድ እሳት፣ ጎርፍ፣ ድርቅ፣ የእርሻ መሬት ጥበት፣ ስደት እና የኑሮ ውድነት ዋነኞቹ የአየር ንብረት ለውጥ ወጤቶችና ተፅእኖዎቹ መሆናቸውንም አስገንዝበዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአምስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ ደን በየዓመቱ የሚጨፈጨፍ መሆናቸውን የጠቆሙት ዶክተር እሸቱ፤ ይህ በዚህ ከቀጠለ ከ27 ዓመት በኋላ ከ200 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ከመላው ዓለም ለመፈናቀል የሚገደዱ ሲሆን አብዛኞቹም ከአፍሪካ መሆናቸውን አመልክተዋል።

ድርጅቱ ከግሎባል አልያንስ ጋር በመቀናጀት በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ላይ ያተኮሩ ስራዎች እንደሚሰራ የተናገሩት ዶክተር እሸቱ፤ የአየር ንብረትን ሊቋቋም የሚችል አረንጓዴና አካታች ሥራ ኢኮኖሚ እንዲፈጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሰራ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ ዶክተር እሸቱ ማብራሪያ፣ ድርጅቱ በጋሞ ዞን ጨንጫ ወረዳ የሚስተዋለውን የመብራት ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል የሶላር ኃይል አገልግሎት ለማስጀመር አቅዷል። እንዲሁም በጨንቻ በወረዳ የሚገኙ ሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የቡላ ምርትን ለማጎልበት እና ገበያ ለመፍጠር የሚሰራም ይሆናል፡፡ ድርጅቱ ለኢትዮያውያን መብት ከአማራ ልማት ማህበር፣ አፋር ልማት ማህበር እንዲሁም የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር ጋር የስትራቴጂክ መግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

ከግሎባል አልያንስ ጋር የስትራቴጂክ ትብብር ስምምነት ያደረገው የአማራ ልማት ማህበር የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ አቶ ደግአረግ ስዩም በበኩላቸው፣ ከግሎባል አልያንስ ጋር የተደረገው ስምምነትም በክልል በሰሜኑ ጦርነት ጉዳት የደረሰባቸውን መሰረተ ልማት በተለይም ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ መልሶ ለቋቋም ያተኮረ ነው። በደቡብ ወሎ ወረባቡ ወረዳ የፈረሰን ትምህርት ቤት መልሶ ለማቋቋም የተደረገ ስምምነት ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር ዋና ስራ አስኪያጅ ዶክተር አለማየሁ መኮንን፣ ከግሎባለ አልያንስ ጋር የሚደረገው ስምምነት የመጀመሪያ አለመሆኑን ጠቅሰው፤ የጤናውን ሥርዓት በተሻለ መልሶ ለመገንባት በሰው ኃይል፣ በተቋማት ግንባታ ያለውን ሰፊ ችግር በዘላቂነት ማገዝን መሰረት ያደረገ ስትራቴጂካዊ ስምምነት መሆኑን ገልጸዋል።

ዜና

# የሰላም ስምምነቱ የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ እየተሰራ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የሰላም ስምምነቱ የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ እየተሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

ኮሚሽኑ ሰሞኑን በልማት አጋሮች መካከል ያለውን የኢንቨስትመንት አጋርነት ለማጠናከር ያለመ ውይይት ባካሄደበት ወቅት፣ የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ዳንኤል ተሬሳ እንደገለጹት፤ የሰላም ስምምነቱ የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡ ለስኬቱም ከተለያዩ አካላት ጋር በመተባበር በልዩ ትኩረት እየተሰራ ነው፡፡

ሰላምና ኢንቨስትመንት ቀጥተኛ ትስስር አላቸው ያሉት ምክትል ኮሚሽነር ዳንኤል፤ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በርካታ የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ከመሥራት ባለፈ ለባለሀብቶቹ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የሰላም ስምምነት መደረጉን ተከትሎ በርካታ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ኮሚሽኑ በዘንድሮው በጀት ዓመት የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ምህዳሩን የማስፋት እና ለባለሀብቶች ሁኔታን ምቹ ከማድረግ አኳያ በርካታ እንቅስቃሴዎች ማድረጉንም ተናግረዋል፡፡



ምክትል ኮሚሽነር ዳንኤል ተሬሳ



የውይይቱ ተሳታፊዎች

ምክትል ኮሚሽነሩ፣ ኢትዮጵያ በ2014 በጀት ዓመት ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት እንደቻለች ገልጸው፤ በአንጻሩም ከውጭ በሚገቡ ምርቶች በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ትኩረት በማድረግ በርካታ የሥራ እድል ለመፍጠር እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የልማት አጋሮችም ቢሆን ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር አብረው ለመስራት ፈቃደኞች መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን ኮሚሽኑ ከልማት አጋሮቹ ጋር የነበረውን ግንኙነት ብሎም አዳዲስ ድርጅቶች ጋርም ለመሥራት የሚያችል ይህን የመሰለ ውይይት ማካሄዱ ጠቃሚ በመሆኑ እንደሚደግፉ አስታውቀዋል፡፡

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ በዚህም ከ 184ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል፡፡ የኢንቨስትመንት አካባቢን ለማሳደግ ብሎም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይም ትኩረት ተደርጓል፡፡ የኢንቨስትመንት ስራዎችን መደገፍና በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ለመግታት በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡

ዘርፉን ለማገዝ በንግድ ትስስር፣ የፈጠራ ስራዎችን በማበረታታት፣ የስራ እድሎችን ለመፍጠር በተለይም የውጭ ንግድን በማስተዋወቅ ረገድ በስፋት እየሰራ ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነር ዳንኤል፤ ዘርፉን ለማሳደግ መሰል የውይይት መድረኮች በቀጣይነት እንደሚደረጉም ጠቁመዋል፡፡

# ክልሉ የሌማት ትሩፋትን እውን ለማድረግ ለእንስሳት እና ንብ ማነብ ስራዎች ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው

**ስምስም መንግሥቱ**

ባህርዳር፡- የአማራ ክልል ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የሚተገበረውን የሌማት ትሩፋት መርሃግብር ለማሳካት ለእንስሳትና የንብ ማነብ ልማት ላይ የአምስት ዓመት እቅድ ቀርጾ በትኩረት እየሰራ መሆኑን የክልሉ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የጽህፈት ቤቱ ምክትል ኃላፊ አቶ ነጋ ይስማው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ክልሉ የማር ምርታማነትን ለመጨመር የአስር ዓመት እቅድ ነድፏል፡፡ የተትረፈረፈ ልማት ለማከናወን ከነደፈው የአስር ዓመት እቅድ የተቀዳ የአምስት ዓመት እቅድ በመቅረጽ የሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብርን ለማሳካት እቅዱን ሕዳር 18 ቀን 2015 ዓ.ም ይፋ በማድረግ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

የሌማት ቱሩፋት መርሃግበሩ ስኬታማነት የተቀረፀው የአምስት ዓመት እቅድ የፌዴራል መንግሥት ያስቀመጠውን አቅጣጫ መሠረት ያደረገ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ነጋ፤ ለሌማት ቱሩፋት መርሃግብሩ ስኬታማነት እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች እንዲሁም በንብ ማነብ የማር ልማት እንደሚጠቀሱና ክልሉም ዘመናዊ የአነባብ ዘዴን በመጠቀም የተትረፈረፈ የማር ልማት በማከናወን ለሀገራዊ እቅድ ስኬት የድርሻውን እንደሚወጣ አስረድተዋል፡፡

ለእቅዱ ስኬታማነትም በክልሉ ከሚገኙ ሰባት ያህል ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ማዕከል እና ጽሕፈት ቤቱ በጋራ ሆነው በክልሉ ያለውን የማር ምርት አቅምና ሀብት የመዳሰስ ሥራ እንደሚጀመር የገለጹት ምክትል ኃላፊው፤ አሁን ላይ ልማቱ የደረሰበት ደረጃ ለማወቅ ሀገራዊ መረጃዎች በመሰብሰብ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት ላይ ትኩረት መሰጠቱን አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ ነጋ ማብራሪያ፣ ለማር ልማቱ የሚያስፈልግ የህብረንብ መጠንና ቀፎዎች እንዲሁም የክሉን የሕዝብ ብዛት መሠረት ያደረገ የጥናት ሥራ ተሰርቷል፡፡ በክልሉ በአነስተኛ ደረጃ በሚከናወነው ባህላዊ ቀፎ እና ባለው የሥራ አጥ ኃይል በመጠቀም ልማቱን ማሳደግ የሚቻልበት ዕድልም አለ፡፡ ለንብ ማነብ ተግዳሮት የሆኑትን በመለየት፣ ለመፍትሄውም በሕግ ማዕቀፍ የታገዘ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ልማቱን ለማጠናከርም እየተሰራ ነው፡፡



አቶ ነጋ ይስማው፤

ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የሚተገበረው የሌማት ቱሩፋት መርሃግብር በግብርናው ዘርፍ በሰብል ልማቱ በስንዴ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ በአቮካዶና በሙዝ መጀመሩ ይታወሳል፡፡

ዓሣን ጨምሮ የእንስሳትና እንስሳት ውጤት እንዲሁም ንብ ማነብ ለሌማት ቱሩፋት እቅድ ስኬታማነት ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ ኋላቀር የአመራረት ዘይቤን ከመቀየር ጀምሮ ዘመናዊና የተሻሻሉ ዝርያዎችን ወደልማቱ በማስገባት በዘርፎቹ ስኬት ለማስመዝገብ ታቅዶ ነው ወደ ሥራ የተገባው፡፡

# የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነጻነት አዋጆችን በአግባቡ መተግበር እንዳልተቻለ ተጠቆመ

**ሃይማኖት ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የመገናኛ ብዙኃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጅን በአግባቡ መተግበር አልተቻለም ሲል ገለጸ፡፡

በኢትዮጵያ ኽዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የመረጃ ነፃነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ማናዬ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመገናኛ ብዙኃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጆች ከዚህ በፊት የወጡ ቢሆንም በተለያየ ምክንያት አዋጆችን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ገልጿል፡፡

ከአዋጆቹ ተቀድተው መውጣት የነበረባቸው ደንቦች እና መመሪያዎች መኖራቸው እና በአስፈፃሚ አካላት ቁርጠኝነት ማነስ የመገናኛ ብዙሃን እና መረጃ ነፃነት አዋጅ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ እልተቻለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አዋጁ እንዲወጡለት የሚጠበቁ አራት ደንቦችና በርካታ መመሪያዎች መኖራቸውን በመጥቀስ እስካሁን እንዲወጡ አለመደረጋቸውን ተናግረዋል፡፡

ከአዋጆቹ ተቀድተው መውጣት ከሚገባቸው ውስጥም እስካሁን ሁለት ደንቦች እና ለደንቦቹም መመሪያዎች መውጣታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከደንብና መመሪያዎች አንጻር ለአዋጁ የሚያስፈልጉት ሁለት ደንቦችና መመሪያዎች አለመውጣታቸው ለሥራው እንቅፋት መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ደንቦቹም አገራዊ ሚስጥራዊ መረጃዎችን እና የሰርተፍኬት አሰጣጥ ሁኔታን በተመለከተ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወስንባቸው ወሳኝ ደንቦች መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

የትኛው መረጃ ምስጢራዊ ነው፤ የትኛው አይደለም የሚለው በደንብና መመሪያ ካልተመለሰ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች መረጃ ይፋ እንዲያደርጉ ሲጠየቁ የሀገር ሚስጢር ነው በሚል ሰበብ እንቅፋት መሆናቸው አይቀርም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህንን መረጃ የማግኘት የዜጎች መብት በግለሰቦች ፍላጎት የተነሳ እንዳይጣስ ለማድረግ የደንቦቹ መውጣት የግድ አስፈላጊ መሆኑንም አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

አቶ ማናዬ በማብራሪያቸው፤ ለእነዚህን ደንቦችና መመሪያዎችን በአንድ ወገን ብቻ ሊወጡ አይችሉም ያሉ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ደንብና መመሪያውን በማዘጋጀት በ2009 ዓ.ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ እንዲሁም በተያዘው ዓመት ባለፈው ጥቅምት ወር እንደገና በማሻሻል ለብሔራዊ መረጃ ደህንነት አስተዳደር ማቅረባቸውን ገልጸዋል። እነዚህ የቀሩ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ጊዜ ይወጣሉ ተብሎ ለመግለጽ እንደማይቻልም አስታውቀዋል።

ከተጠቀሱት ደንቦችና መመሪያዎች ውጪ ሌሎች መመሪያዎች ወጥተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ ለአብነትም የሰነድ አያያዝና አጠባበቅ፤ የሥልጠና ማንዋል መመሪያ፣ ለሕዝብ መረጃ አሰጣጥና ይፋ ማድረጊያ መመሪያዎች ወጥተው ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሚገኙም ጠቅሰዋል፡፡

ካልወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በልተናነሰ መጠን ለአዋጁ ተፈጻሚ አለመሆን ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ያለው የአስፈጻሚዎች ቁርጠኝነት ማነስ መሆኑንም ገልጸዋል።

አስፈጻሚዎች በተቋሙ የሚሰጡ ምክረ ሃሳቦችንና ትዕዛዞችን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ትልቅ ክፍተት መኖሩን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ምክር ቤቱም አዋጁን ከማውጣት ባለፈ የአዋጁን ተፈጻሚነት ተከታትሎ ከመጠየቅ አንጻር ውስንነት እንዳለበትም አብራርተዋል።

የመገናኛ ብዙሃን እና መረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 የወጣው በ2000 ዓ.ም ሲሆን፤ አዋጁ ሲወጣም ዋና ዓላማው በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 12 ላይ የተደነገገውን ግልፅ የመንግሥት አሰራርና ተጠያቂነትን ማስፈን እንዲሁም የሕዝቡን ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነትን ማረጋገጥ ነው።

# ዜና

## “በዲፕሎማሲ ከተመዘገቡት ድሎች ባሻገር ስነበሩ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ዶክተር ዲማ፤ በተለይ ሩሲያና ቻይና ባይኖሩ ኖሮ በኢትዮጵያ ላይ የሚጣል ማዕቀብ ከአቅም በላይ መሆኑና ይህ ደግሞ በዲፕሎማሲ ረገድ ብዙ ሥራ መሰራ እንዳለበት ያመላክታል ብለዋል፡፡

ከአጼ ኃይለሥላሴ በኋላ የመጡ የኢትዮጵያ መንግሥታት የአገርና የሕዝብ ጥቅም ወደጎን በመተው ሥልጣን ላይ እንዲቆዩ የሚያስችላቸውን ግለሰባዊ ዲፕሎማሲ ስልት ሲከተሉ እንደነበር የጠቆሙት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው፤ የዲፕሎማሲ ውስብስብነት በኢትዮጵያም ሆነ በየትኛው ዓለም የተለመደ ክስተት ነው ብለዋል፡፡ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከተከሰተው ጦርነት ጋር ተያይዞ የውጭ ዓለም ለአንድ ወገን አድልቶ በሀገሪቱ ላይ ያሳረፈው የዲፕሎማሲ ጫና የሚያሳየው በቡድኖች ለሃገር ሳይሆን ራስን ሥልጣን ላይ ለማቆት ሰፊ ዲፕሎማሲ ሥራ መስራቱን ነው፡፡ ነገር ግን የዲፕሎማሲ ሥራ ዛሬ የተጀመረ ጉዳይ ስላልሆነ በአገሪቱ ላይ ለደረሱ ጫናዎች ብዙ ምክንያቶች ከማቅረብ ክፍተቶችን መፈተሹ በእጅጉ ይጠቅማል ብለዋል፡፡

የዲፕሎማሲ ሥራ ውጤታማ የሚሆነው ከቡድን እና ከሌሎች አላስፈላጊ ግድፈቶች በጸዳ መልኩ በኮታ ሳይሆን በእውቀትና በክህሎት የተሻሉ ዲፕሎማቶች ወደ ዘርፉ ሲመጡ ነው ያሉት ፖለቲከኛው፤ ከዚህ አንጻር በኢህአዴግ ጊዜ የቋንቋ ችሎታቸውና ስለ ዓለም ያላቸው እውቀት ታሳቢ ሳይደረግ በኮታና በፖለቲካ ወገንተኝነት የተመረጡ ዲፕሎማቶችን መልሶ ለዲፕሎማሲ ሥራ ማሰማራት የራሱ አሉታዊ ተጽእኖ እንደነበረው አልሸሸጉም፡፡

በንጽጽር በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ ወርቃማ ዲፕሎማሲ እንደነበራት የጠቀሱት ዶክተር ዲማ ፤ ለዚህም ንጉሱ ጠንካራ ዲፕሎማቶችን በመምረጥ በውጭ አገር በማሰልጠን ወደ ሥራ በማሰማራታቸው ምክንያት እንደነበር ተናግረዋል፡፡

አሁንም ቢሆን የነበሩ አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት ስምምነት ላይ መድረስ ትልቅ ምዕራፍ ቢሆንም የስምምነቱ ተግባራዊነት ገና በመሆኑ በጦርነቱ ሂደት ውስጥ በተፈጸሙት የወንጀል ድርጊቶች ላይ የተጠያቂነት ሥርዓት ከመዘርጋት ጋር ተያይዞ ብዙ ጫናዎች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በጥቅሉ የነበሩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ በሀገር ውስጥ አስተማማኝ ሰላም ለማስፈን የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረስ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ዲማ፤ በውጭ ደግሞ የተሻሉ ዲፕሎማቶችን በማሰማራት በተቻለ መጠን ከሁሉም ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ጠቃሚ መሆኑን መክረዋል፡፡



## ባይደን...

ግንኙነት በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት አሜሪካ አዲስ የተመሰረተውን የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና እድልን ለመጠቀም ትልቅ ስምምነት ማድረጓን አብስረው፤ ይህ ስምምነት በርካታ የአሜሪካ ድርጅቶች እድሉን ተጠቅመው በቀጠናው ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

ይህ ትልቅ እድል ነው፤ እድሉም ለአፍሪካ መጻኢ ተስፋ የሚሰጥ ነው። ወደ ተግባር እንዲቀየርም አሜሪካ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ታደርጋለች ብለዋል። ይህም በተለይ አፍሪካና አሜሪካ ያላቸውን ግንኙነት የበለጠ እንዲጠናከር የሚያደርግ ነው ሲሉ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል አሜሪካ በአፍሪካ ቀጠናዊ ንግድ እንዲስፋፋ ጥረት እያደረገች ስለመሆኑ ያነሱት ፕሬዚዳንት ባይደን፤ በተለይ ለንግድ ስራ አመቺነት የሚረዳ የመሰረተ ልማት ግንባታ ሀገራቸው ትኩረት ሰጥታ እየሰራች መሆኑን አንስተዋል።

የእርሳቸው አስተዳደር ከመጣ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ሚሊኒየም ቻሌንጅ ኮርፖሬሽን በተሰኘ ድርጅት አማካኝነት አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በአፍሪካ ሀገራት ማስተዋወቁን አንስተዋል። ይህ ኮርፖሬሽን በቀጣይ ዓመታትም በአፍሪካ ተጨማሪ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ እንደሚያደርግ ይጠበቃል ብለዋል።

በተጨማሪ አሜሪካ በአፍሪካ አህጉር ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች እንዲመጡ በኢኖቬሽንና ስራ እድል ፈጠራ ላይ የምታደርገውን ድጋፍ ትቀጥላለች ያሉት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፤ አገራቸው በአፍሪካና በአፍሪካውያን ላይ የምታደርገው ኢንቨስትመንት አይቋረጥምም ብለዋል።

በቢዝነስ ፎረሙ ላይ 300 በዘርፉ የሚገኙ የአፍሪካና አሜሪካ የቢዝነስ ድርጅቶች የተሳተፉ ሲሆን በቀጣይ አብሮ ለመስራት የሚያስችላቸውን ስምምነትም አድርገዋል።

## ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ያሳትን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ዐቢይ አሕመድ በአሜሪካ- አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ተገኝተው ሰፊ የዲፕሎማሲ ስራ እያከናወኑ ነው። በአሜሪካ ቆይታቸው የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት እንዲጠናከርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ወዳጅነትና ትብብር እንዲጎለብልት ትልቅ ስራ እየሰሩ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከንና ከብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ጋር የኢትዮጵያና የአሜሪካ የቆየ ግንኙነት ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መክረዋል።

የውይይቶቹ ትኩረቶቹ በሁለትዮሽ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ቢሆንም አካባቢያዊ ጉዳዮችንም የቃኘ ነው። በሁለትዮሽ ውይይቱ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈጠረው የሰላም ስምምነት አንደኛው የትኩረት ዘርፍ ነበር። ስምምነቱ እውን እንዲሆን የአሜሪካ መንግሥት ላሳየው አጋርነት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምስጋና አቅርበዋል። በኢትዮጵያ በኩል በፖለቲካና በተለያዩ ዘርፎች የተጀመሩ የማሻሻያ ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ፍላጎት እንዳለ መገለጹንም ተናግረዋል።

ቃል አቀባዩ እንዳብራሩት፤ ኢትዮጵያና አሜሪካ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በዴሞክራሲና ግንባታና ሽብርን በመዋጋት ረገድ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ የቆየ ጠንካራ ወዳጅነት ያላቸው አገሮች ናቸው። በአንዳንድ ጉዳዮች የሃሳብ ልዩነቶች ቢገጥሙም ለዘመናት የቆየውን ወዳጅነት የሚለውጥ አይደለም። ጉባኤውም ይህን የቆየ ወዳጅነት ይበልጥ ለማጠናከር እድል የሰጠ ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ የአጉዋ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስረዳት የተቻለበት መድረክ ነው። በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከዓለም ባንክና ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከፍተኛ ሃላፊዎች ጋር ኢትዮጵያ የጀመረችው የዳግም ግንባታና መልሶ ማቋቋምን በተመለከተ የገንዘብ ድጋፍ በሚገኝበት ሁኔታዎች ላይ ውይይት ማድረጋቸውንና ውጤት መገኘቱን ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ አለም ገለጻ፤ በሌላ በኩል ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ካደረጉ የአውሮፓ ኅብረት አገራት አምባሳደሮችና ተወካዮች ጋር ውይይት አድርገዋል። የአውሮፓ ኅብረት የኢትዮጵያን ልማት የሚደግፍ ተቋም መሆኑንና ኢትዮጵያ ከድህረ ጦርነት በኋላ ወደ መልሶ ግንባታ መግባቷን፤ የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራች መሆኑን በመግለጽ ከኅብረቱ ጋር ያላት ወዳጅነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ፍላጎት እንዳለ ተገልጾላቸዋል። ከመልሶ ግንባታ አንጻር ተቋሙ እገዛ እንዲያደርግም ጠይቀዋል። የአውሮፓ ኅብረትና የአባል አገራት ተወካዮችም ዘላቂ ሰላም ማምጣት ጦርነት ከማካሄድ የከበደ መሆኑን እንረዳለን የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ገልጸዋል። የሰላም ግንባታ ሂደቱን መደገፍ ቅድሚያ እንደሚሰጠው፣ ለኢትዮጵያ ትኩረት እንደሚሰጡና የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት ለአውሮፓ አስፈላጊ እንደሆነ መግለጻቸውን ተናግረዋል።

ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲን አስመልክቶ ቃል አቀባዩ እንደገለጹት፤ ከ3 ሺህ በላይ ዜጎች ከሳውዲ አረቢያ መመለስ ተችሏል። ዛምቢያ ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ የሚያጣራ ቡድን ወደ አካባቢው ይሰማራል፤ በተመሳሳይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመራ ቡድን ማላዊ ሄዶ በዜጎች ላይ የደረሰውን ሁኔታ ለማጣራት ጥረት እያደረገ መሆኑንና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ትልቅ አካባቢያዊ ስጋት በመሆኑ በዘላቂነት ለመፍታት የሁሉም ጥረት አስፈላጊ መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል።

## ታሪፍ ባልወጣለት መንገድ ምክንያት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የትራንስፖርት ታሪፍ ያልወጣለት በመሆኑ ለአላስፈላጊ ወጪ እና ለእንግልት መዳረጋቸውን የሚዛን ከተማ ነዋሪዎች ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተናግረዋል።

ተለዋጭ መንገዱ ታፍ ስላልወጣለት ከሚዛን ከተማ ወደ አዲሱ ገበያ ለሚደረግ ጉዞ 15 ብር ይከፍሉ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው በአሁኑ ወቅት ከ50 እስከ 70 ብር ለመክፈል መገደዳቸውን ኗሪዎቹ ተናግረዋል።

አማራጭ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎቶች አለመኖራቸውም ችግሩ እንዲባባስ እንዳደረገው ገልጸዋል። የሚዛን ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሽዋንግዛው ዓለሙ የታሪፉ መጨመር እና የትራንስፖርት አለመኖር ኅብረተሰቡን እንዳማረረው ገልጸው፤ መንገዱ ሲጠናቀቅም ቢሆን የሚቆጣጠር የመንግሥት አካል ባለመኖሩ ታሪፉ አሁን ባለው ሁኔታ ሊቀጥል ይችል ይሆናል ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል።

የከተማዋ ነዋሪ ተማሪ ቃልኪዳን በበኩሏ፤ የትራንስፖርት አለመመደብና ተለዋጭ አገልግሎት እየሰጠ በሚገኘው መንገድ ታሪፍ አለመውጣቱ ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ ተጽዕኖ እያሳደረባቸው መሆኑን ገልጻለች።

ሌላው የሚዛን ከተማ ነዋሪው ወጣት አማኑ ታደሰ፤ ማህበረሰቡ በትራንስፖርት ወጪ ምክንያት በኢኮኖሚ እየተዳከመ መሆኑን ገልፆ፤ ትራንስፖርት እንደልብ ባለመገኘቱ በግል ድርጅት ተቀጥሮ የሚሰሩ ሰዎች ከስራ እየተስተጓጎሉ መሆኑን ተናግሯል።

በተጨማሪም ወደ አካባቢው የተመደበ የብዙኃን ትራንስፖርት አማራጭ ባለመኖሩ ሕዝቡ ከትራንስፖርት ታሪፍ ውጪ ከመክፈል ባለፈ አማራጭ የለውም ያለው ወጣቱ፤ መንግሥት ኅብረተሰቡ እንደ አማራጭ ሊጠቀምባቸው የሚችል የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን ሊመድብ እንደሚገባ ጠቁሟል። በተጨማሪም አሁን ባለው ሁኔታ የትራንስፖርት ስምሪቱ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል ሲል አሳስቧል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድጅት የኅብረተሰቡን ቅሬታ በማንሳት ያነጋገራቸው የጉለሌ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ቅርጫፍ ጽህፈት ቤት ስራ አስኪያጅ አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ፤ በነዋሪዎች የተነሳው ቅሬታ ትክክል መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በነበረው ታሪፍ ከአዲሱ ገበያ ሚዛን 15 ብር እንደነበረ ጠቅሰው ሆኖም አሁን ከአዲሱ ገበያ ፍተሻ ያለው መንገድ እየተሠራ በመሆኑ ታክሲዎች ከአዲሱ ገበያ ሽሮሜዳ እንጦጦ ያለውን አማራጭ ተለዋጭ መንገድ እንዲጠቀሙ ተገድደዋል። ይህ ደግሞ በሚጓዙት መንገድ ላይ የ10 ኪሎ ሜትር ብልጫ ያለው መሆኑን አብራርተዋል።

በመሆኑም ተለዋጭ መንገዱ የ10 ኪሎ ሜትር ርዝመት ከነባር መንገዱ ብልጫ መኖሩን በማረጋገጥ የትራንስፖርት ታሪፍ የማውጣት በሂደት ላይ መሆኑን ተናግረዋል። ታሪፉ በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ብቻ የሚወሰን አለመሆኑን ጠቅሰው ለሱሉልታ ከተማ ልዩ ዞን አስተዳደር ትራንስፖርት ጽህፈት ቤት ታሪፍ እንዲያወጣ ልኬቱን አሳውቀናል ብለዋል። ሆኖም የሱሉልታ ከተማ ልዩ ዞን አስተዳደር ትራንስፖርት ጽሕፈት ቤት ታሪፍ ማውጣት እንደማይችል እደገለፀላቸው እና ታሪፉ የሚወጣው በኦሮሚያ ትራንስፖርት ቢሮ መሆኑን አሳውቀውናል ሲሉ ገልፀዋል።

ከአዲስ አበባ ሚዛን የተመደበ የብዙኃን ትራንስፖርት አማራጭ አለመኖሩን የተናገሩት አቶ ሳሙኤል፤ የኅብረተሰቡ ፍላጎት እየጨመረ ሲመጣ ድጋፍ ሰጪ ተሽከርካሪዎችን ሊመደቡ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

መንገዱ ሲጠናቀቅ ታሪፉ አሁን ባለው ይቀጥላል ለሚለው የነዋሪዎች ስጋትም አቶ ሳሙኤል ምላሽ ሰጥተዋል። ነባር መንገዱ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የጠበቀ ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ ስጋት ሊገባው አይገባም ብለዋል። ከታሪፍ በላይ እንዲከፍሉ በሚጠየቁበት ጊዜም ለቁጥጥር ሰራተኞችና በቢሮ ነጻ ስልክ ደውለው ሪፖርት ማድረግ እደሚችሉ ኃላፊው መልእክት አስተላልፈዋል።

በተለዋጭ መንገድ ምክንያት የመንገዱ ርዝመት እንደጨመረ መረጃው ደርሷችሁ ለምን የታሪፍ ማስተካከያ ልታደርጉ አልቻላችሁም ስንል የጠየቅናቸው የሱሉልታ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ኃላፊ ወይዘሮ ትግስት በላይ በበኩላቸው፤ ተለዋጭ መንገድ ሲሰራ አሰሪ አካሉ ከጽህፈት ቤታቸው ጋር ተገናኝቶ መፍትሄ ማስቀመጥ እንደነበረበት ገልጸው፤ ከዚህ ቀደም ከሱልልታ አዲሱ ገበያ ያለውን ታሪፍ የሚያወጣው የኦሮሚያ ትራንስፖርት ቢሮ በመሆኑ እና የሱሉልታ ከተማ ትራንስፖርት ታሪፍ ማውጣት ስለማይችል ችግሩ ሳይፈታ እንዲቆይ አድርጎታል ብለዋል።

በቁጥጥር በኩል አመርቂ ውጤት ማምጣት አለመቻላቸውን ያመኑት ወይዘሮ ትዕግስት፤ የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ የቁጥጥር ክፍተት መኖሩን ገልጸዋል።

ሆኖም የኅብረተሰቡ የቅሬታ ምንጭ የሆነውን አዲሱ ገበያ ፍተሻ የሚገኘውን ተለዋጭ መንገድ ልኬት አከናውነው ኪሎ ሜትሩን ለከተው ታሪፍ ማውጣት እንደሚችሉ በክልሉ አቅጣጫ መቀመጡን ጠቅሰው፤ በተከናወነው ልኬት መሰረት አዲስ ታሪፍ ተግባራዊ መደረግ እንደሚጀመር ተናግረዋል። አዲሱ ታሪፍ ሲወጣም ቁጥጥሩ ተጠናክሮ እንደሚሰራበትና ችግሩ በአጭር ጊዜ እንደሚፈታ ወይዘሮ ትዕግስት አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጉባዔው የኢትዮ - አሜሪካን ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ምቹ ዕድል የሚፈጥር ነው!

የአሜሪካ አፍሪካ መሪዎች ጉባኤ በአሜሪካ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በጉባኤውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች መሪዎች ተገኝተዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጉባኤው ጎን ለጎን ከአሜሪካና ከዓለም አቀፍ ተቋማት መሪዎች ጋር መክረዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን መረጃ ዋቢ ያደረጉ መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአሜሪካ እየተሳተፉበት ያለው የአፍሪካ አሜሪካ ስብሰባ ሰፊ ዲፕሎማሲ ስራ ለመስራት እድል የሰጠ ነው። በዚህም መንግሥት ለሰላም ያለውን ጥረት በዓለምአቀፍ ደረጃ ለመግለጽ ዕድል አግኝቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን እንዲሁም ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የደህንነት አማካሪ ጋር የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል ውይይት አድርገዋል። በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን አሜሪካ ላደረገችው ድጋፍ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አድናቆት እንዳላቸው መግለጻቸውንም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጠቁሟል፡፡ የአሜሪካና የኢትዮጵያ የቆየ የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲጠናከር እንደሚሰሩም ተወያይተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአሜሪካ የንግድ ተወካይ አምባሳደር ካትሪን ታይን ጋር የሁለቱን ሀገራት የንግድ ግንኙነት ማስፋት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ጥሩ ውይይት ማድረጋቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡

የአሜሪካ አፍሪካ መሪዎች ጉባኤ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከጉባኤው ጎን ለጎን ያካሄዷቸውና እያካሄዷቸው የሚገኙ ውይይቶች የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ወደ ቀደሞ መልኩ እንዲመለስ ለማድረግ የበኩሉን ሚና ሊወጣ እንደሚችል ይታመናል፡፡

ኢትዮጵያ ጠንካራ ግንኙነት ከምታደርግባቸው ሀገሮች መካከል አሜሪካ አንዷ ናት፡፡ ሁለቱ አገሮች ከአንድ ምእተ ዓመት የተሻገረ ግንኙነትም አላቸው፡፡ አገሮቹ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን፣ በተለያዩ መስኮችም ጠንካራ ግንኙነቶች እንዳላቸው ይታወቃል፡፡

በንግድ በኩል ያላቸው ግንኙነትም ጠንካራ የሚባል ሲሆን፣ በፈረንጆቹ 2021 ከፍተኛ መጠን ያለው የኢትዮጵያ ምርት አሜሪካን መደረሻ ማድረጉን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚሁ ዓመት ከሶማሊያ ቀጥሎ ኢትዮጵያ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያገኘችው ወደ አሜሪካ ከተላኩ ምርቶች ነው፡፡ በተጠቀሰው ዓመት 330 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ምርቶች ወደ አሜሪካ ገበያ ተልከዋል፡፡

ሁለቱ አገሮች ሽብርተኝነትን በመዋጋት በኩልም ስትራቴጂክ አጋርነት አላቸው፡፡ በዚህም በሶማሊያ መሽጎ ጎረቤት ሀገሮችን ከማሸበር በተጨማሪ የአካባቢው እና የዓለም ስጋት ሆኖ የቆየውን አልሸባብ በጋራ በመዋጋት ቡድኑ እንዳሻው እንዳይሆን ማድረግ ችለዋል፡፡ አሜሪካ ከሰሀራ በታች ላሉ የአፍሪካ ሀገሮች ከቀረጥ ነጻ ምርቶቻቸውን ወደ አሜሪካ ገበያ እንዲያስገቡ ከሰጠችው እድል /አጎአ/ እስከ አለፈው ዓመት ድረስ ኢትዮጵያም ተጠቃሚ ነበረች፡፡

አሜሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን የሚኖሩባት ሀገር መሆኗ ይታወቃል፤ ትምህርትን፣ ሥራን ብለው በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከፍተኛ ነው፤ በየዘመኑ የተነሱ የኢትዮጵያ መንግሥታት በኢትዮጵያውያን ላይ ግፍ ሲፈጽሙ ኢትዮጵያውያን ለመጠለል ከሚሄዱባቸው ሀገሮች አንዷ አሜሪካ ናት፡፡

ይህ ሁሉ የሁለቱ ሀገሮች ግንኙነት ትሩፋት ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ትሩፋቱ ግን ከአንድ መቶ ዓመት በላይ የዘለቀ ግንኙነት ላላቸው ለእነዚህ ሁለት ሀገሮች የሚመጥን ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡ ይህ ግንኙነት በተለያዩ ጊዜያት በተነሱ የአሜሪካ መንግሥታት ጫና የበዛበት አቋም የተነሳ የሚፈለገውን ያህል ርቀት የተጓዘ አይደለም፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ በሁለቱ አገሮች መካከል አንዳንዴ የሚከሰቱ መሻከሮች ግንኙነቱ ባለበት እንዲቀጥል እንኳ እድል የሚነፍጉ ሆነው ቆይተዋል፡፡

ለእዚህም በሰሜን ኢትዮጵያ ሲካሄድ የነበረውን ጦርነትና የአባይ ግድብን ተከትሎ ከግብጽ ጋር ባሉ አለመግባባቶች ሳቢያ የሻከረውን የሁለቱን አገሮች ግንኙነት በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በግንኙነቱ ላይ መጥፎ ጠባሳ አሳርፈዋል፡፡ በተለይ የሰሜን ኢትዮጵያን ጦርነት ተከትሎ አሜሪካ የወሰደችው አቋም በሁለቱ አገሮች መካከል ዘመናትን የዘለቀውን ግንኙነት ታሳቢ ያደረገ አልነበረም፡፡ ይህ የአሜሪካ አቋም አሜሪካ ከሰሀራ በታች ላሉ የአፍሪካ አገሮች በፈቀደችው ከቀረጥ ነጻ እድል የኢትዮጵያ ምርቶች ወደ አሜሪካ ገበያ እንዳይገቡ አድርጓል፡፡

እነዚህ ጉዳዮች የሁለቱ አገሮች ግንኙነቶች መጠናከርና መታደስ እንዳለበት ያመለክታሉ፡፡ ግንኙነቶቹ ለሁለቱ ሀገሮችም ሆነ ለሕዝቦቻቸው ወሳኝ ናቸውና መጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡

አሁን ደገሞ ነገሮች ተቀያይረዋል፤ ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ በሚል መርህ በአፍሪካ ኅብረት አወያይነት በደቡብ አፍሪካ በኢፌዴሪ መንግሥትና በሕወሓት መካከል በተካሄደው የሰላም ስምምነት የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት በሰላማዊ አማራጭ መፍትሄ እያገኘ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በሰላም ስምምነቱ መሰረት ሰፊ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እንዲደርስ እያደረገች ትገኛለች፤ በጦርነት የወደሙ መሰረተ ልማቶችን በመጠገን እንደ ስልክ መብራትና የመሳሰሉት አገልግሎት እንዲመለሱ እያደረገች ናት፡፡ ባንኮችና ትምህርት ቤቶችም አገልግሎት ለመጀመር እየሰሩ ናቸው፡፡

እነዚህን የኢትዮጵያ ጥረቶች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይ ለአሜሪካ ማስረዳትና ማሳየት ይገባል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የአሜሪካ ቆይታም ለዚህ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጉባኤው ጎን ለጎን ከአሜሪካ ባለሥልጣናት ጋር ያደረጓቸው በቀጣይም የሚያደርጓቸው ውይይቶች ፋይዳ ከፍተኛ ነውና፡፡

የኢትዮጵያና አሜሪካ ግንኙነት ታሪካዊ መሰረት ያለው ብቻ ሳይሆን ህያውና ጠንካራ ሊባል የሚችል እንደመሆኑ በቀጣይም ሊጠናከር የሚችለበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ ዋናው ነገር ኢትዮጵያ ከአገሮች ጋር ያላት ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ትፈልጋለች፡፡ ይህ ጽኑ አቋሟ ነው፡፡ ከአሜሪካም ጋር ያላት ግንኙነት በዚሁ ላይ የተሰመረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

ቀጣዩ የሁለቱ አገሮች ግንኙነትም ይህንን የኢትዮጵያ አቋምና ረጅም ዘመን የዘለቀውን የሁለቱን አገራት ግንኙነት ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል!


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለሰላም ስምምነቱ ተገዥ በመሆን ሕዝብን ከስቃይ፤ አገርንም ከውድቀት መታደግ ያስፈልጋል

**ወጋሶ**

የሰው ልጅ ሕይወትን በአፋጣኝ ከሚቀጥፉ ምክንያቶች ዋነኛው ተጠቃሽ ጦርነት መሆኑ እምብዛም አከራካሪ አይሆንም። ጦርነት ካለ በአገርም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የተወጠነ በጎ ተግባርን ከግብ ማድረስ አይታሰብም። የተያዘን የረጅም ጊዜ እቅድ ለመተግበር ቀርቶ ዕለቱን በሰላም ውሎ ለማደር ይቸግራል።

ከዚህ በመነሳትም አገራት ጦርነት እንዳይገጥማቸው ከባላንጣዎቻቸው በኩል የሚያጋጥማቸውን አለመግባባት በተቻላቸው ሁሉ በሰላማዊ መንገድ በዲፕሎማሲ ለመፍታት ይጥራሉ። ከአቅም በላይ ሆኖ መግባባት ላይ መድረስ ሳይችሉ ቀርተው ወደጦርነት የሚገቡበት አጋጣሚ የሚፈጠር ከሆነ ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰላም ለማውረድ የየራሳቸውን እርምጃ ሲወስዱ ይስተዋላሉ።

ለዚህም ምክንያቱ ጦርነት አውዳሚ፤ አጥፊም መሆኑ ነው። በተለይ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች እንዲህ አይነቱ ጉዳይ ሲገጥማቸው ፈተናው የጎላ ይሆንባቸዋል። ሊያስከፍላቸው የሚችለውም ዋጋ ከፍ ያለና በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው አይነት

ለዚህም ነው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ተገዶ ወደጦርነት በገባው በፌዴራል መንግስትና በሕወሐት መካከል፤ በደም አፋሳሹ ጦርነት የሚጠፋውን ሕይወት መታደግ የሚያስችል የሰላም ስምምነት የተደረሰው። የሰላም ስምምነቱ ላይ የመደረሱ ፋይዳ የመጀመሪያው የሰው ልጅ ሕይወት እንዳይጠፋ በዋናነት የላቀ ሚና ሲኖረው፤ በመቀጠልም በግጭት ምክንያት ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ለተጋለጡ ወገኖች እርዳታ በማድረስ የሚታደጋቸውን እድል መፍጠር ስለሚያስችል ነው።

ከዚህም ጋር ተያይዞ መንግስት የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ በማድረግ እየሄደበት ያለው መንገድ ይበል የሚያሰኝ ነው። ከስምምነቱ ማግስት ጀምሮ የሰብዓዊ እርዳታ ወደ ትግራይ ክልል መጓጓዝ መጀመሩ ለክልሉ ህዝብ እፎይታን የፈጠረ ነው።

በግጭቱ ምክንያት የእለት የምግብ እርዳታ ለሚፈልጉ ዜጎ ዕርዳታውን በተሻለ መንገድ ማቅረብ እያስቻለ ነው። መድሃኒትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ሸቀጦችን ወደ ክልሉ ለማድረስ የሚደረገውም ጥረት እየፈጠረ ያለው እፎይታ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር በመንግስት በኩል ያለውም ቁርጠኝነት ሕዝቡ የሰላም ትሩፋቱ ተጠቃሚ እንዲሆን እያደረገው ይገኛል።

ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተደረሰው የሰላም ስምምነት አማካኝነት ነው። በወቅቱም ስምምነት ከተደረሰባቸው ጉዳዮች መካከል ግጭትን በዘላቂነት ማቆም፣ ሰብዓዊ እርዳታን ያለገደብ ማድረስ፣ በአገሪቱ ህገ መንግስት መሰረት ሕግና ስርዓትን ማስከበር እንዲሁም የሕወሓት ታጣቂዎችን ትጥቅ ማስፈታት የሚሉት ዋና ዋና ነጥቦች መሆናቸው የሚታወስ ነው።

ዓመታት ሲካሄድ የነበረው የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት የብዙዎችን ሕይወት ያሳጣና እንደአገርም ብዙ ዋጋ ያስከፈለ መሆኑ የሚታወቅ ነው። በዚህ መልክ መቀጠሉ አገርና ህዝብን የማያተርፍ በመሆኑ ወደሰላም ስምምነት መምጣት መቻሉ እሰይ የሚያሰኝ ነው። ስምምነቱን ተከትሎም የፌዴራል መንግስት በወሰደው አፋጣኝ እርምጃ ሰብዓዊ እርዳታ ያለገደብ ወደ ክልሉ እንዲገባ በመደረግ ላይ ይገኛል።

መንግስት፣ የሰብዓዊ እርዳታን በተመለከተ ከዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት ጋር በመሆን እርዳታው ለሚያስፈልጋቸው አካላት ያለምንም መዘግየት ለማድረስ መግባባት ላይ መድረሱ ብቻ ሳይሆን የተደረሰበትን ስምምነት ሳያስተጓጉል እያከናወነው ይገኛል።

በተመሳሳይ በክልሉ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በደረሰው ውድመት ከጥቅም ውጭ የሆኑትን መሰረታዊ አገልግሎቶች በመጠገን ተመልሰው ለአገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ በተቻለው ፍጥነት ሁሉ በመጠገን ላይ ይገኛል።

የሰብዓዊ እርዳታውን ብቻ ብንመለከት መንግስት እስከ ታህሣሥ 2 ቀን 2015 ዓ.ም በትግራይ ክልል ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ከ98 ሺ ሜትሪክ ቶን በላይ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ የሰብዓዊ እርዳታ መሰራጨቱን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በቅርቡ ከገለጸው መረጃ ለማወቅ ይቻላል። በክልሉ ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች ያልተገደበ የሰብዓዊ ድጋፉ እየደረሰ መሆኑም እየተገለጸ ይገኛል።

በተለይ ምግብ እና አልሚ ምግብን ጨምሮ ከ89 ሺ 217 ሜትሪክ ቶን በላይ የሰብዓዊ እርዳታ መሰራጨቱን ከኮሚሽኑ የወጣው መረጃ ያመለክታል። እየደረሰ ካለው የሰብዓዊ እርዳታ ውስጥ የመንግስት ድርሻ ፣ ከ13 ሺ 686 ሜትሪክ ቶን በላይ እንደሆነም ይታወቃል።

ወደ ትግራይ ክልል በሚጓጓዘው መድሃኒት በኩል ያለው መረጃ እንደሚያስረዳው ከአንድ ሺ 222 ሜትሪክ ቶን በላይ ነው፤ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎችን በተመለከተ ሰባት ሺ 651 ሜትሪክ ቶን መሰራጨት ተችሏል። በተመሳሳይ ለስራ ማስኬጃና ለፕሮግራም ማስፈጸሚያም የሚውል ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ መላኩን ከኮሚሽኑ የወጣው መረጃ ያሳያል። በተመሳሳይ ነዳጅን በተመለከተ ከ690 በላይ ሊትር ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል ወደ ክልሉ መጓጓዝ ተችሏል።

በዚህ መልክ መንግስት በስምምነቱ ወቅት እተገብራለሁ ብሎ መግባባት ላይ የደረሰባቸውን ነጥቦች ከስምምነቱ በኋላ አንድ በአንድ እየተገበረ ይገኛል። በዚህ ጽሑፍ ማንሳት የፈለግኩት የሰብዓዊ እርዳታውን የተመለከተ ብቻ በመሆኑ ሌሎች ነጥቦችን ለጊዜው አልጥቀሳቸውም እንጂ በእነርሱም በኩል መንግስት በቁርጠኝነት እየሰራ ስለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በእርግጥ፣ የሰላም ስምምነቱ ተጀምሮ ይፋ ከመሆኑ በፊት በትግራይ ክልል በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ አስቸኳይ የሰብዓዊ እርዳታ እንደሚሻ የእርዳታ ድርጅቶች ደጋግመው ሲገልጹ መቆየታቸው የሚዘነጋ አይደለም። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችም አፋጣኝ የምግብ እርዳታ ጠባቂ መሆናቸውንና ለረሃብ መጋለጣቸውንም እነዚሁ ዓለም አቀፍ የተራድኦ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ ባወጧቸው መረጃዎች ሲጠቃቅሱ እንደነበር አይካድም።

ይህ ብቻ አይደለም ዓለም አቀፍ ተቋማት እና መንግሥታት የፌደራል መንግሥቱ እና የሕወሓት ኃይሎች ግጭቱን አቁመው ለድርድር እንዲቀመጡ በተደጋጋሚም ጥሪ ሲያቀርቡ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።

ምንም እንኳ ቁጥራቸው የተጠበቀውን ያህል እና እነርሱ ምቹ ሁኔታ ካገኙ እርዳታውን ለማድረስ ሲገልጹ እንደነበረው አይነት አይሁን እንጂ በአሁን ወቅት ከ20 በላይ የሚሆኑ አጋር አካላት በትግራይ ክልል እየተከናወነ ባለው የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት ላይ የየበኩላቸውን ለማድረግ እየተሳተፉ እንደሚገኙ ይታወቃል።

የሰብዓዊ እርዳታውን መንግስት ብቻውን የሚተገብረው እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው፤ ጉዳዩ የሁሉንም ርብርብ ይሻል። በተለይም በአገር ውስጥ ያሉና በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መንግስት በዋናነት እየሰራ ያለውን ተግባር በመደገፍ በኩል ያላሰለሰ ጥረት ቢያደርጉ ሕዝብን ከስቃይ አገርንም ከውድቀት በመተባበር መታደግ ይቻላል። በመንግስት በኩል እየተሰራ ያለው ስራ ቃሉን አክባሪ የሚያስብል ነው፤ ልክ እንደ መንግስት ሁሉ በሕወሓት በኩል የተገባው ቃልም ተፈጻሚነቱ በሕዝብ ዘንድ ሊሰማም፤ ሊታይም ይገባል ባይ ነኝ።

# ነፃ ሃሳብ

# ልጅህ ከአንተ በተሻለ የሕይወት መርህ እንደሚገዛ አስተውለህ ታውቃለህ!

በመክሊት ወንድወሰን

ስገምት ማን ማንን ነው የሚበልጠው? እንደው ልጄን አባትህን እኮ ትበልጠዋለህ ብላ ልታሳምፅብኝ ይሆን እያልክም እያሰብክ ይሆናል። ደግሞ የእኔ ልጅ በምኑ ነው እኔን የሚበልጠው? የቀረበለትን ምግብ እንኳን አስተካክሎ አይጎርስም እኔው ነኝ ሸምቶ ከማምጣት እስከ ጠቅልሎ ማጉረስ ሚናውን የምጫወተው ትልም ይሆናል።

ከእኔ ውጭ መሰረታዊ ፍላጐት እንኳን የለውም። ያለማንም ከልካይ እኮ የቃል ስልጣኔን አስፈፅምበታለሁ። ውጣ ብዬ አስወጣዋለሁ ግባ ብዬ አስገባዋለሁ ፈጣሪን ካልፈራሁ ደግሞ እንደ እንዝርት ላሾረው እችላለሁ። አእምሮህም እንደው በምን ይሆን የሚበልጠኝ ብሎ በእድሜ ይሆን ኸረ አይሆንም እሱ እኮ ልጄ ነው።

በገንዘብ? ምን እያልኩ ነው የገንዘብ ስር አልባነት እና እንዴት ተሁኖ እንደሚመጣ እንኳን መረዳት ተስኖት ስወጣና ስገባ አባቴ ያንን ግዛ ይሄንን አምጣ ያንን አውጣ እያለ እያሰቃየኝ ነው።

በትምህርት ይሆን እንዴ? አይ አይ እሱም አይሆንም የኔ ልጅ እኮ ገና መዋዕለ ህፃናት ተማሪ ነው እኔ ደግሞ በ 1983 ነው 12ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቅኩት።

መቼም የፈለገ ጊዜ ቢራቀቅ ዘመኑም ቢዘምንም ምንም እንኳን እኔም ትምህርቱን ካቆምኩ ሶስት አስርት አመታት ቢያልፍም እንደው ምንም ቢሆን የዛሬው የመዋዕለ ህፃናት ተማሪው ልጄ አይበልጠኝም..." አልሽኝ አይደል ? እኔ ግን እልሀለሁ ካንተ ማነፃፀሪያዎች በተለየ ማወዳደሪያ ልጅህ ይበልጥሃል። አይበልጠኝም ካልክ እናሲዝ ብዬ ትንሿን ጣቴን አውጥቻለሁ። እነሆ ወዳጄ ልጅህ በምን እና እንዴት ካንተ እንደሚበልጥ እንዲህ እያልኩ አስረዳሀለሁ።

በመጀመሪያ ልጅህ ካንተ በተሻለ ትሁት ነው። በትላንትናው ድሉ አይኩራራም የዛሬንም ውድቀቱን እያብሰለሰለ ነገውን በጭጋግ ውስጥ አያይም። የትኛውንም ነገር ይሞክራል ካቃተው አንተ አባቱ ከሱ እንደምትሻል በማሰብ ርዳታህን እንድትቸረው ቀኝ እጁን ይዘረጋልሀል። "ምን ይለኝ ይሆን ? ባለመቻሌ ይታዘበኝ ይሆን?" አይልም እንደማይችል ከገባው ያንተን እርዳታ ይጠይቃል።

ከዘጠኝ ወር እስከ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ያለ ልጅ ለመቆም ሲንገዳገድ ታየዋለህ ካቃተው ተንፏቆ በመሄድ ያገኘውን ነገር ተደግፎ ይቆማል። መቆሙን ካረጋገጠ በኋላ ያንኑ የተደገፈውን ነገር ሳይለቅ ለመሄድ ይሞክራል። ይሄ ከተሳካለት ሁሌ ተደግፌ ካልሄድኩ አይልም ያለ ማንም እርዳታና ድጋፍ ራሱን ችሎ መቆምን ይፈልጋል። ምናልባት ግን ወገቡና አጥንቶቹ ስላልጠነከሩ ይወድቅ ይሆናል።

በሚገርም ሁኔታ ግን ዛሬ ወድቄአለሁ ብሎ ነገ አልነሳም፣ አልቆምም፣ አልሄድም አይልም። ነገም ይሞክራል። ነገ ሲሞክር ግን ከዛሬ በተሻለ መቆምን ይማራል። ይኸው ያንተው ልጅ በራሱ መቆምን ከተማረ በኋላ ያንን ብቻ እንደ ስኬት አይቆጥረውም፤ ካልሄድኩ ካልሮጥኩ ይልሃል።

እጁን ይዘኸው ራሱ መሄድ አይፈልግም አምልጦክ ሊሮጥ ይከጅለዋል። መቆሙ ብቻ አያረካውም ያንተ ወፌ ቆመች እያሉ ማጨብጨብም አኩራርቶት በቃ መቆሜ በቂ ነው ይኸው ተጨብጭቦልኛል አይልም። ያንተን ማሞካሸት ብቻ በማየት ከነገው ርምጃው እና ሩጫው መቅረት አይፈልግም አድናቆትህ አያስኮፍሰውም መሄድ እና መሮጥ ለሚባሉ ነገሮች መነሻ እንጂ መድረሻ እንዳልሆነ ደመነፍሱ ይነግረዋል።

ያንተን ልገምት አለቃህ እንድትሰራ የሚሰጥህን ስራ ላንተ ደሞዝ መከፈል ምክንያት የሆነን ስራህን እንኳን ልትሰራ ፈቃደኛ አይደለህም። አንድ ቦታ ላይ ቆመሃል። ተደግፎም ለመሄድ አትፈልግም በራስክ መቆም ካቃተህ ተደግፎ መሄድ እንደሚሻል አታስብም። ክብርህን የምታስነካ ይመስልሃል፤ ራስህንም ችለህ አትሄድም መቆምህ ብቻ አኩርቶሃል።

የስራ ወንበር መያዝህ በራሱ ስኬት መሆኑ ይታይሃል። አንተ ቆመሃል ዘመኑ ዘምኗል ጊዜውም ነጉዷል። ሁሉም ይሮጣል አንተ ግን ቆመሀል። መሄድና መሮጥ እንዳለብህ እንደ ልጅህ ደመነፍስህ ብቻ ሳይሆን ዓይነ ህሊናህም እንዳይነግርህ ስኬት ማለት ስራ መያዝ እና እንዳይባረሩ በስራ ሰዓት መግባት መውጣት መሆኑን ለአመታት አስጠንተህው እሱም አብሮህ ቆሟል።

ልጅህ የሚማር አዕምሮና የሚምር ይቅርታ የሚያደርግ ልብ አለው። በሚማረው አዕምሮው አንተን ይጠይቃል። ጥሩ ወላጅ ከሆንክ አሁንም ትመልሳለህ። የሚያስገርመው ነገር ግን አንተ መልስ ያልቅብሃል እንጂ የእርሱን ጥያቄ ስትመልስ ብትውል አያልቅም።

አንድ የማውቀውን ነገር ሳጫውትህ አንተም እንደሱ ነበርክ። ቤተሰቦችህ ላይ የጥያቄን ጎርፍ ያለምንም ርህራሄ የምታፈስ። ግን ምን ያደርጋል በወላጆችህ የመልስ አልበኝነት ወይም ስልቹነት ይህንን ዋነኛ የአዕምሮ ማጎልበቻ የሆነውን የመጠየቅ ባህልህን ወስደው ጠይቆ መረዳትን እንደ የበታችነት ስሜት እንድትቆጥረው ያደረጉክ።

አንድ ወዳጄ እንደውም ምን ይላል “አላውቀውም አስረዱኝ ስትሉ አንዴ ብቻ ነው እንደ አላዋቂ የምትቆጠሩት ከዛ ቀን በኋላ ግን ካለማወቅ አረንቋ ትላቀቃላችሁ። ሰው ምን ይለኛል ብላችሁ ባትጠይቁ ግን ለዘላለም ላለማወቅ ጨክናችኋል” ይላል።

ቤተሰቦችህ ስትጠይቃቸው አንተ ልጅ ነህ። አሁን ከትልቅ ሰው ጋር እያወራሁ ነው። አትጨቅጭቀኝ ስራ ይዣለሁ። ውጣና ተጫወት። እሱን ስታድግ ትደርስበታለህ በሚሉ አዕምሮን በሚያቀጭጩ መልሶች ነው ለዚህ ያበቁክ።

ታዲያስ አንተስ ምንህ ሞኝነው ከቤተሰቦችህ በወረስካት ልምድ ልጆችህ በጥያቄ ልብህን ሲያወልቁህ «ስታድግ ትደርስበታለህ» በምትል አጭር አረፍተ ነገር አስፈላጊ ሆኖ ስታገኘው መቸረጥ አድርገህ ለልጅህ ትጠቀማታለህ።

አሁንም ግን እልሃለሁ ልጅህ ከአንተ ይሻላል ስለማያውቅ አለማወቁን አውቆ አዋቂ ነኝ የምትለውን አንተን ከመጠየቅ ባስ ሲልም ከመሞገት አይመለስም። ስንቶቻችን አዋቂ ሰዎች ነን ግን የማናቀውን ነገር አላውቅም ብለን ለማወቅ የምንጥረው?

እኔ ግን በብዙ የሕይወት ተሞክሮዬ ውስጥ ያስተዋልኩት ነገር ብዙ አዋቂ (በዕድሜ) የሚባሉ ሰዎች ስለማያውቁት ነገር ሲጠየቁ አላውቅም ከማለት ይልቅ ከነገሩ ጋር የማይያያዝ ምላሽ ይሰጡሃል። እኔ እኮ ማለት የፈለኩት አሁን አንተ ከመለስከው ምላሽ ጋር ተያያዥነት የለውም ወይም ጥያቄዬ ካልገባህ...... ምናምን ብለህ ሳትጨርስ ፊታቸው መቀየር ይጀምራል ከዚያም አቂመውብህ ያርፉታል።

አንተም እኔም እንደዚህ አይነት ነገር ሲገጥመን ስቀን አዎ ይሆን ይሆናል ብለን የሰዎችን ስሜት ጠብቀን እናልፋለን። ልጅህ ግን ስለ አንተ ስሜት አይጠነቀቅም። መልስህ ልክ መስሎ ካልታየው አንተ በንዴት ጨርቅህን ትጥላለህ እንጂ እሱ ከመጠየቅና ስህተት መሆኑን ከመግለጽ ወደ ኋላ አይልም።

አንተም አዋቂ የሚለውን የወል ስምህን ላለመጣል ብለህ አላውቅም የኔ ልጅ ነገ ከሰው ጠይቄ፣ ከመጽሐፍ አንብቤ ዘመኑ ጥሩ ነው ከድረ ገጽ አይቼ እመልስልሃለሁ አትለውም። ከፊትህ ዞር እንዲል ብቻ ምክንያት ፈጥረህ ታባርረዋለህ ባስ ሲልም በቁጣ ታሸሸዋለህ። ምክንያቱም አንተም እንደዚህ ተደርገህ ነዋ ያደግከው።

ልጅህ ከአንተ በተሻለ የሚምር ልብም አለው። መቼም እንደሚታወቀው አብዛኞቻችን

> **ዛሬ ወድቄአለሁ ብሎ ነገ አልነሳም፣ አልቆምም፣ አልሄድም አይልም። ነገም ይሞክራል። ነገ ሲሞክር ግን ከዛሬ በተሻለ መቆምን ይማራል**

ኢትዮጵያውያን በተለይም ከተሜዎቹ ከጎረቤት ጋር ነው የምንኖረው እናማ ያው ሰው ከሰው ጋር ሲኖር ይጋጫል አይደል። ይህ አይነቱ ግጭት በልጆች ላይም ይከሰታል።

ረጅሙን ሰዓታቸውን አብረው እንደመዋላቸው ማለትም በትምህርት ቤት ከዚያም ሲመለሱ ደግሞ በሰፈር ጨዋታ ስለሚገናኙ የሚያጋጫቸው ነገር አይጠፋም። ይኸው ግጭት ሲከፋ አንዱ አንዱን እስከ መማታት ሊደርስ ይችላል። የሚደንቀው ነገር ግን አዋቂ የሚባሉት የልጆቹ ወላጆች በዚህ ግጭት ላይ ያላቸው ሚና ነው።

ለልጆቻቸው ተደርበው ከሌላኛው ወላጅ ጋር ይጣላሉ። የኔ ልጅ ጨዋ ነው ያንቺን ነገረኛ ልጅ አሳርፊ የማታሳርፊ ከሆነ ግን...የሚልን ዛቻ ሳይቀር ይለዋወጣሉ። ግጭቱ ውሎ አድሮ ተደጋግፎ በሚኖሩ ቤቶች የሚኖሩ ሁለት ጎረቤታሞችን የፈጣሪን ሰላምታ እንኳን እንዳይለዋወጡ አድርጎ ዓመታትን ሊያስቆጥሩ ይችላል።

የሚገርምህን ነገር ልንገርህ ልጅህ ከጓደኛው ጋር በተጣላ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ታርቆ እንደውም አንተ ተጎድቷል አልቅሷል ብለህ ማባበያ የገዛህለትን ከረሜላ ሳይቀር ካንተ ተደብቆ አካፍሎታል። አንተ ግን ቂምህን አልረሳ ብለህ አንድ አደጋ ቢደርስብህ አለኝ ከምትላቸው ወዳጅ ዘመዶች ሁሉ ቀድሞ የሚደርስልህን ጎረቤትህን መቻል ይቅርታ ማድረግ ተስኖህ ተኳርፈዋለህ። ልጅህን ከተጣላው ምናልባትም ካቆሰለው ጓደኛው ጋር ስታየው ጸጉርህ ሊቆም ወይ ደግሞ ቆሽትህ ሊያር ይችላል።

ነገር ግን እሱ ያንተ ልጅ አዋቂ ነኝ ባይ አላዋቂ አይደለም። እሱ ልጅ ብቻ ነው። ልጅ ደግሞ አያቄምም። የምሩን ይምርና ወደ ቀጣዩ ምእራፉ አንድም የቀድሞ ዶሴ ሳይዝ ከነገው ጋር ይገናኛል። ለዛም ይመስለኛል አብዛኛውን ጊዜ ጨጓራና ደም ግፊት የያዘው ህፃን ልጅ አይተን የማናውቀው። አንተም ከበሽታህ ለማገገም ለመዳን የምትችለው ውስጥህ ያለውን የቂምና የጥላቻ ቋጠሮን ስትፈታ ብቻ ነው። ስለዚህ ወዳጄ እንደሚበልጥህ ልጅህ ሁን ስል እመክርሃለሁ።

ብዙ ጊዜ መታዘብ ከቻልክ ልጅህ ለሳቅ እና ለደስታ ቅርብ ነው። የአንድ ብር ጣፋጭ ገዝተህ ብትሰጠው ልቡን በሀሴት ትሞላዋለህ። የምር ደስታውን ከፊቱ ላይ ሲያበራ ታስተውላለህ ባለው ነገር መደሰትን ያውቃል። አንተ ግን እጅህ ላይ ያለው ነገር ብዙሃን ሰዎች ጋር እንደሌለ አታስተውልም።

ባለህ ነገር ሳታመሰግን ሌላ ነገር ትፈልጋለህ። እሱን ስታገኘው መልሶ ይቀልብህና ያስጠላሃል። ነፍስህን ጥቂት ጊዜ ሀሴት እንድታደርግ እንኳን አትፈቅድላትም። ሁሌ የጎደለብህና የሌለህ ነገር ብቻ ይታይሀል። ያለህ ነገር ዋጋው አይታይህም ለዚም ነው ደስታ ካንተ የራቀው።

ልጅህ በእግሩ ከትምህርት ቤት እስከ ቤት ከጓደኞቹ ጋር እየተጫወተ እየተላፋ ይመጣል። ምን ያህል ኪ.ሜ እንኳን እንደሄደ አያስተውልም። ደስ እያለው ስለሚጓዝ ጸሐዩ አቧራው መንገዱ ርቀቱ አይታወቀውም። አንተስ? የመስሪያ ቤት ሰርቪስ ሰፈርህ አድርሶ ለምን ቤቴ ደጃፌ ድረስ አያደርሰኝም? አንድ ፌርማታ እንዴት በእግሬ እሄዳለሁ ደስ ሲለው ብቻ ስራ ለሚገባው የኛ አለቃ እኮ መኪና ተሰጥቶታል።

ድሮም እዚህ መስሪያ ቤት...ትላለህ። አንተ አንድ ፌርማታ ብቻ እንድትሄድ ነው የተደረገው፤ ነገር ግን አንተ በዛው ሰርቪስ ውስጥ ሆነህ በትራንስፖርት ማጣት ምክንያት በበጋ ጸሐዩ በክረምት ዝናብ የሚፈራረቅበትን ረጃጅም ሰልፍ ላይ ያለውን ሕዝብ አትመለከትም ብታይም አንተ ስለእነርሱ ግድ የለህም። ያ የረጅም የታክሲ ወረፋ የድርጅትህን ሰርቪስ እንድታመሰግን ምክንያት አይሆንህም።

ለራስህ ደስታን እና ሳቅን ለመፍጠር ፍቃደኛ አይደለህም ያለህን የሚያሳይ ዓይን ሳይሆን በጎዶሎህ የሚወቅስህ ሕሊና ብቻ ነው ያለህ። ህጻናት ግን እንዲህ አይደሉም ባላቸው ነገር ይደሰታሉ ። ለዚህም ነው ብዙ አዋቂ ሰዎች ላይ የሚታየው የጭንቀት በሽታ እምብዛም ህጻናት ላይ የማይስተዋለው።

ልጅህን ንጹህ ልብስ አልብሰኸው አየር ለመቀበል ትንሽ ከሰፈር ወጥታችሁ ብትሄዱ እመነኝ ይህ ቀን ከልጅህ የልብ ጽላት ላይ ተጽፎ ለዘላለም ይቀራል። በቀጣዩም ቀንም ለጓደኞቹ እኔና አባቴ እኮ በዚህ መንገድ ስንሄድ ይህንን አይተን ያንን አልፈን እያለ የሚያወራው ታሪክ ትሰጠዋለህ።

በዚያ ሰዓት ግን ምናልባትም አንተ ከልጅህ ጋር እየሄድክ የሚታይህ ውሃ ልማት ንጹሕ ውሃ ለማቅረብ የቆፈረው ጉድጓድ አይተህ ምን እንደው እዚህ አገር በተቆፈረው ጉድጓድ ወድቀን ወጌሻ ጋር እንድንሄድ አስበው ነው እንዴ የሚሰሩት እያልክ እየተማረርክ ይሆናል።

ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሲቆፈር አማርረህ መሠረተ ልማቱ ሳይኖር አማርረህ እንዴት ሕይወትን ትገፋዋለህ? በእነዚህ ሁሉ ነጥቦች ልዩነታችሁን ዘርዝሬ ታዲያ አሁንስ ልጅህ ካንተ አይሻልም? አይበልጥህም ? መልሱን ላንተው ተውኩት።

# በአገር ወግ ለአገር መድረስ

ጽጌረዳ ጫንያለው

እመጫት ናት፤ ለያውም አንድ ሳምንት ላይ ያለች። ሆኖም የምትሰራው ካገኘች ወደ ኋላ አትልም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ያጠራቀመችው ቤሳ ቤስቲን የሌላት መሆኑ፤ የሚያርሳትና ጎዶሎዋን የሚሞላላት ወገን፤ ዘመድ አለመኖሩ ነው። ስለዚህም መታረስን እያማራትም ቢሆን ጥላው ወደ ስራ ማቅናት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የእለት ጉርሷ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው።

ዮርዲኖስ አሰፋ እንደዛሬው ወልዳ በቤት ሳትቀመጥ ሰው ቤት በተመላላሽ ሰራተኛነት ታገለግል ነበር። በዚህም ለእርሷም ሆነ ለልጇ ጉሮሮ አንሳ አታውቅም። ባለቤቷ ትቷት ሲሄድ ግን ነገሮች ለጊዜው ጨለሙባት። የምታደርገውም ግራ ገባት። ብዙ ነገሮችም ከበዷት። ሆኖም ዝም ብላ ግን አልተቀመጠችም። ህመሟን ቻል አድርጋ ጎንበስ ቀና ማለቱን ተያያዘችው እንጂ። ለመብላት መሥራት፣ ልጇንና እርሷን ለማኖር መፍጋት ግድ ነውና ያለምንም ምርጫ ያገኘችውን ትሰራም ነበር።


ነብሰጡር ሆኖ፣ ማልዶ ወጥቶ ምሽት ላይ ወደቤት መመለስ እጅግ ፈታኝ የሆነባት ዮርዲኖስ፤ ልጇን አዝላ ጭምር ነበር ሥራ የምትሄደውም፤ የምትሰራውም። አንዳንዴ ልብስ እያጠበች በምትቆይበት ጊዜ ከጀርባዋ አውርዳው እንዲጫወት ታደርገዋለች። ይህ ግን የባሰውን መከራ የሚያበላት ነበር። ምክንያቱም ሳታስበው ከስሯ ጠፍቶ ይሄዳል። እናም እርሱን በመፈለግ ጊዜዋን ታጠፋለች። የዚህን ጊዜ አሰሪዎቿም ይናደዱባታል።

‹‹ጉሮው ጠብ ሳይል በዚህ አይነት ፈተና ውስጥ ራስን ማኖር እጅግ ከባድ ነው። ነገር ግን ምርጫ ሳይኖር ምን ማድረግ ይቻላል›› የምትለው ዮርዲኖስ፤ ፈተና ቢኖረውም ትናንትን ታግላ አሸንፈዋለች። ዛሬን ግን ልትቋቋመው በምትችለው ደረጃ ላይ አይደለችም። የብዙዎች እጅ ካልተዘረጋላት ጊዜውን ማለፍ ከብዷታል። ምክንያቱም ዛሬ ከእርሷና ከልጇ ሌላ አዲስ ነፍስ ተጨምሯል። ለያውም ብዙ ነገር የሚያስፈልገው። እንደ አገራችን ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት እስካሁን ለአራሷ የተደረገላት እንክብካቤ ባይኖርም የምታጠባ ነችና እንክብካቤ ሊደረግላት ግድ ነው። ግን ማን ያድርገው ነው ጥያቄው? መተጋገዝን ሀሳባቸው ያደረጉ ባህላችንን ዳግመኛ ለማለምለም የተነሱት ድንቅ የኢትዮጵያ ልጆች ይህንን ከሚያደርጉት መካከል ናቸው። ስማቸው “የኢትዮጵያ ልጆች የእርስ በእርስ መተጋገዝ ማህበር” ይባላል። ቀደምት እናቶቻችንና አባቶቻችንን ያስታውሱናል። “በምን?” ከተባለ፣ በ’ርስ በ’ርስ መተጋገዝ ሲሆን፤ ወደ ጎዳና ለመውጣት ጫፍ የደረሱ ሰዎችን በማገዝ ይታወቃሉ። እንዴት ከተባለ ደግሞ ፈቃደኞችን በመሰብሰብና ድጋፋቸውን በቀጥታ ለችግረኞች እንዲሰጡ በማድረግ ነው። ለአብነት “አምስት ዳቦ ለአንድ ቤተሰብ” በሚል የጀመሩት ፕሮጀክት ከ75 ቤተሰብ በላይ ተጠቃሚ ያደርጋሉ። ይህ ሲሆንም ወረዳው የመለመለላቸውን ሰው ከዳቦ ቤት ባለቤቶች ጋር በማስተሳሰር በቀን አምስት ዳቦ እንዲወስዱ በማድረግ ነው።

ከዚህ ዳቦ ጠቀሜታ አንጻር ባለታሪካችን ዮርዲኖስ የምትለው ነገር አላት። ‹‹ልጄ ሦስት ዓመት የሞላው በቅርቡ ነው። እናም ትምህርት ቤት አልገባም። ስለዚህም ከእግሬ ስር ስለማይጠፋ በራበው ቁጥር ዳቦ ይለኛል። እናም ብዙ ጊዜ አስር ብር ይዤ ሽገር ዳቦ እሰለፋለሁ። ይሁንና ሳላገኝ የምመለስበት ቀን ብዙ ነው። የዚህን ጊዜ ለልጄ ምን መመለስ እንዳለብኝ ግራ ይገባኛል። ልጄ ሲያለቅስ እንባውን መጥረግ እንኳን አልችልም። ስለዚህም ሁልጊዜ እድሌን አማርረዋለሁ፤ አለቅስም ነበር።

“ፍሰጡር ስሆን ደግሞ ብዙ ልብስ በአጠብኩ ጊዜ በጣም ይርበኛል። ማንንም ስጡኝ ስለማልል እየራበኝ ሥራውን አጠናቅቃለሁ። ከዚያም የሚብሰው ቤት ልግባ እንጂ የምቀምሰው ነገር ስለማይኖር በድካሜ የተነሳ ምግብ ማዘጋጀት አልችልም። ይህ ደግሞ ብዙ ጊዜ አቅቶኝ እንድወድቅ አድርጎኛል። እናም የነበርኩበት ስቃይ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። አሁን ግን ሁሉ ነገር ተቀይሯል። በእነርሱ እገዛ ልጄም ማልቀስ አቁሟል። እኔም ብሆን ረሀቤን አስታግሼ እንደልቤ ቤቴ ገብቼ ምግብ በማዘጋጀት ልጄንም እኔንም ስመግብ ቆይቻለሁ። ዳቦውን በመስጠታቸው መጀመሪያ የልጄን እንባ ጠረግሁ። በመቀጠል ደግሞ መንገድ ላይ ሲርበኝ እየተመገብሁ ረሀቤን ገታሁ። ቤት ስገባም ብርታት ስለሚሰጠኝ ድካሜን እንድረሳ ሆንኩ።›› ትላለች የበጎ አድራጎት ማህበሩን ሥራ ሰብዓዊነት ስታስረዳ።

ዮርዲኖስ ቀጣይ ሕልሟ በቅርቡ ተነስታ ሥራዋን መጀመር ሲሆን፤ የተሻለ ሥራ ሰርታ ለእርሷ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም መትረፍ ነው። በተለይም በጎ አድራጎት ማህበሩ ሌሎችን ሲያግዝ በተለያየ መልኩ ስለሆነ እንደ



ወይዘሮ ዮርዲኖስ አሰፋ

ፎቶ:- ሐዲስ አብርሃ



አቶ ሸዋንግዛው በሻህውረድ

እነርሱ ከእርሷ ላነሱ ሰዎች መድረስ ትፈልጋለች። ከእነርሱ እርዳታ እራሷን አውጥታ በምትችለው ሁሉ እነርሱን ለመምሰልም ታልማለች። ምክንያቱም በእርሷ እምነት ሰው ሰውን የሚያግዘው ስላለው ብቻ አይደለም። ‘ከአለው ነገር ሲያካፍልና እርስ በእርስ ሲተጋገዝ ተረዳዳ እንለዋለን’ የሚል አቋም አላት።

ሌላው ባለታሪካችን አይነስውሩ አቶ ሸዋንግዛው በሻህውረድ ሲሆኑ፤ አራት ልጆቻቸውን ያለ እናት የሚያሳድጉና የሚያስተምሩ ናቸው። ቀደም ብሎ እንደዛሬው አይነስውር ሳይሆኑ የሬሳ ሳጥን በመስራትና በመሸጥ ይተዳደሩ ነበር። የአበባ ሥራም በእጅጉ ይችላሉ። እናም ደስተኛ ሆነው ዓመታትን አሳልፈዋል። ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ግን አንድ ትልቅ አሳዛኝ ነገር ገጠማቸው። መከታና ተንከባካቢ፣ ጧሪና ቀባሪ ትሆነኛለች የሚሏትን የበኩር ልጃቸውን በሞት ተነጠቁ። በዚህም እጅጉን አዘኑ። ጠዋት ማታም እዬዬ ሆነ ሥራቸው። ነገሮች ሁሉ ተስፋ እያስቆረጧቸው ሥራቸውን በአግባቡ እማያከናውኑበት ደረጃ ላይ ደረሱ።

ይህ ከባድ ሀዘን ደግሞ ተደራራቢ መዘዝ ይዞባቸው መጣ። “መሥሪያዬ …” የሚሉትን መሪና የፈለጉት ቦታ ላይ የሚያደርሳቸውን ዓይናቸውን አሳጣቸው። በአጠራቀሙት ገንዘብ ያልሞከሩት ህክምና አልነበረም። ዓይንዎት ጉዳት ደርሶበታል ተብለው ከዓይን ባንክ ወጥቶ ሌላ ዓይን እስኪተከል ድረስ ደርሰዋል። ነገር ግን ይህም ሆኖ የጠበቁት አልተገኘም። የተተከለው ዓይን ለተወሰነ ጊዜ ብርሃን ሆናቸው እንጂ አልዘለቀም። የባሰ ትንሹን ብርሃን ጨምሮ አጠፋው። በእርግጥ እዚህ ላይ አንድ ነገር ያነሳሉ። ከብራቸውም፤ ከዓይናቸውም እንዳይሆኑ ያደረጋቸው የሐኪሙ ሁኔታ እንደሆነ ያምናሉ። ምክንያቱም ሌሎች ዓይናቸው የተቀየረላቸው ሰዎች ዛሬ ድረስ እያዩ ነው። እናም በእድላቸው እንጂ በህክምናው አያማርሩም።

አቶ ሸዋንግዛው በደረሰባቸው የጤና ችግር ምክንያት ልጆቻቸውን ሰርተው መመገብ እንዳይችሉ ሆነዋል። አሁን በዳበሳ ነው ሁሉን ነገር የሚያከናውኑት። ከሰል ለማቀጣጠል እንኳን ጎረቤት ለምነው ነው። ከዚያ የልጆቻቸውን ዓይን ዓይናቸው አድርገው ምግብ ያበስላሉ። ጠዋት ቀስቅሰው ትምህርት ቤት ከላኳቸው በኋላም ማታም እንደተለመደው ይቀበሏቸዋል። እንደውም መንግስት ጠዋትና ማታ ባይመግብላቸው ኖሮ ሁሉ ነገር እንደሚጨልምባቸው ያነሳሉ። እርሳቸው ማታ ለእራት ብቻ ያበስላሉ። የኢትዮጵያ ልጆች የእርስ በእርስ መተጋገዝ በጎ አድራጎት ማህበር እጅ ባይታከልበት ደግሞ ይህም አይሳካም ነበር።

ማህበሩ ከችግሮቻቸው ቅድሚያ የሰጠው ለቤታቸው ጉዳይ ሲሆን፤ ከሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ ጋር በማስተሳሰር ቤታቸው እንዲሰራላቸው አድርጓል። ከዚያ ደግሞ የቤት ውስጥ አስቤዛ ያቀርብላቸዋል። በዚህም ‹‹የልጆቼ እናት ነው›› ይሉታል የማህበሩን ሥራ ሲያስረዱ። በተለይም ከቤታቸው መታደስ ጋር ተያይዞ ‹‹ቤቱ ጎርፍ ነበር፤ አራቱም ልጆቼ በአንድ ላይ ተኝተው ሁልጊዜ ያበሰብሳቸዋል። በዳበሳ ሳያቸው እንደረጠቡ ነው። ብዙ ጊዜ ቅዝቃዜው የበረታ ስለሚሆን ሳል አያስተኛቸውም። እናም በአይነስውርነት አቅሜ ጾድቷል፣ አልጸዳም ሳልል አጥቤ አደርቃለሁ። አንዳንዴ ዝናቡ ሲበረታና ልብሱ መድረቅ እንደማይችል ሳምን ጨምቄ አለብሳቸዋለሁ። በተለይ ክረምት ለእኔም ሆነ ለልጆቼ የፈተና ጊዜ ሆኖ ያልፋል። ማህበሩ ከሰራልኝ በኋላ ግን ሁለት ሁለት ሆነው ዝናብ ጠብ ሳይልባቸው እንቅልፋቸውን ይተኛሉ። አሁን ደስተኛ ሆነው፣ እኔንም ወደ ማገዝ ገብተውልኛል። ስለዚህም እነዚህን በጎ ሰሪዎች አምላክ ያብዛልን እያልኩ ሁሌ እመርቃለሁ።›› ይላሉ።

አቶ ነፃነት ጣሰው የኢትዮጵያ ልጆች የእርስ በርስ መተጋገዝ በጎ አድራጎት ማህበር ፕሬዝዳንት ናቸው። ማህበሩ በከፋ የድህነት ችግር ውስጥ ያሉ ወላጆችን ለልመና ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ተረባርቦ ማገዝ የኢትዮጵያዊያን ባህል ነው። ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ ይህን ባህል የሚሸረሽሩ በርካታ ነገሮች በመታየት ላይ ናቸው። ማገዝ በበዓል ብቻ እስኪመስል ድረስ ብዙዎች ተግባራቸውን ወደዚያ አዙረዋል። ይህ ደግሞ እየጨመረ ያለውን የከፋ የድህነት ችግር በቀላሉ መቅረፍ አያስችልም። እናም “ማህበሩ የሰው ልጅ የሚመገበው ቀን በቀን በመሆኑ እገዛውም ቀን በቀን መሆን አለበት” የሚለውን አላማው አድርጎ እንደተነሳ ይናገራሉ።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወደ ጎዳና ለልመና እየወጣ ያለው የወላጆች፣ የአረጋዊያንና የሕፃናት ቁጥር እንደ አገር አስጊ ደረጃ ላይ ደርሷል። ነገር ግን ከዚህ ችግራቸው ሊያወጣ የሚችል ሥራ በተለያዩ አካላት እየተሰራ ቢሆንም ለውጡ ግን እጅግ አዝጋሚ ነው። ምክንያቱም ጎዳና የወጡ ሰዎች ልምዳቸውን በቀላሉ አይተውምና መደላደሎች ቢኖሩም ተመልሰው ይወጣሉ። ስለሆነም ማህበሩ የተለየ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለበት አምኖ ወደ ተግባር ገብቷል። ከተግባራቱም አንዱ በሕግ የተመራ የጎዳና ልመናን ክልከላ ማድረግ ሲሆን፤ ሌላው በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ ዜጎችን ወደ ጎዳና ሳይወጡ በአሉበት ማገዝና እንዲለወጡ ማስቻል ነው። የእርስ በእርስ መተጋገዙ ደግሞ ይህንን በብዙ መንገድ ውጤታማ ያደርገዋል።

የእርስ በእርስ መተጋገዝ ለኢትዮጵያዊያን አዲስ አይደለም። ባህልም፣ ሃይማኖትም፣ እሴትም ነው። ስለዚህም ለዘመናት ሲከውኑትና ሲኖሩት የቆዩት ነገር ነው። ያ ነገራቸው ደግሞ ዛሬ ድረስ መኖሩን የሚያሳዩን በርካታ ተግባራት ያሉ ሲሆን፣ አንዱም አግዙ፣ እርዱ ሲባሉ ካላቸው ላይ መስጠታቸው ነው። ይሁንና አስተዋሽ ግን እንዲፈልጉ ሆነዋል። ምክንያቱም የእኛ ያልሆኑ ባህሎች ተቀላቅለውናልና ነው። ዛሬ “የ(ለ)እኔ ብቻ” በሚል አስተሳሰብ ውስጥ ያለ ሰው ተበራክቷል። ሆኖም “… ጭራሽ ጠፍቷል” ማለት አይቻልምና ማህበሩ አስተዋሽ፣ አስተሳሳሪ በመሆን ተግባሩን ለመከወን ወስኗል። እያደረገውም ይገኛል ብለውናል።

የማህበሩ ሥራ ድርጅቶችን፣ አከፋፋዮችንና ባለሀብቶችን ከችግርተኞቹ ጋር በማስተሳሰር ሕይወታቸውን በዘላቂነት መለወጥ ነው። ምንም አይነት የውጪ ድጋፍን አያስተናግድም። ‹‹የአገር ልጅ የማር ጠጅ›› የሚለው መርህ ይከተላል። ዋና አላማውም ለወገኖቹ ደራሽ ወገን መሆኑን ማሳየት ነው። በተለይም የእርስ በእርስ መተጋገዝ ባህልን ማጠናከርና የአገራችንን ችግር በጋራ መፍታትን ላይ ያተኩራል። ለዚህ ደግሞ በእየለቱ የሚሰራ ሥራ መኖር አለበት። ሥራው ደግሞ ከተናጠል ይልቅ በጋራ ቢተገበር ይጠቅማልና ማህበሩ ይህንን እየተገበረ ነው።

ወላጆች፣ አረጋዊያንና ህፃናት ለጎዳና ላይ ልመና ሲዳረጉ አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ፆታዊ ጥቃት ይዳረጋሉ። ይህንን ማህበራዊ ችግር በጥናት ላይ በተመሰረተ መልኩ ድጋፍና እገዛ ማድረግ ካልቻልን አደጋው እንደ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን እንደ አገርም የከፋ ይሆናል። በመሆኑም ህብረታችን በእርስ በእርስ መተጋገዛችን መታየት አለበት የሚሉት አቶ ነጻነት፤ ማህበሩ ዓመት እንኳን ያልሞላው መሆኑንም ይናገራሉ።

ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ሰዓት በ“አምስት ዳቦ ለአንድ ቤተሰብ” ፕሮጀክት ክፍለ ከተማው መልምሎ በሰጣቸው መሰረት ማህበሩ 75 የቤተሰብ አባላትን ያግዛል። ከዚህም ባሻገር 10 የክልል ከተሞች ላይ ‹‹የጎዳና ላይ ልመና ይቁም፤ የሕግ ክልከላ ይኑረው፤ የማህበራዊ ኤጀንሲ ፈንድ ተቋቁሞ የተቸገሩ ሰዎች በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ይግቡ›› በሚሉ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት ሲያደርግ ቆይቷል። ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በህብረት በመስራትም ጥናቱ በደንብ እንዲዳብር የተለያዩ ሀሳቦችን እያሰባሰበ ይገኛሉ። በቅርቡም የጥናቱን ውጤት ይፋ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመምከር ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ልጆች የእርስ በርስ መተጋገዝ በጎ አድራጎት ማህበር በ15 ሰዎች የተጀመረ ሲሆን፤ አሁን የተለያዩ የእምነት አባቶችን፣ ምሁራንና ባለድርሻ አካላትን በበላይ ጠባቂነት አስቀምጦ ከአራት ሺህ የሚበልጡ አባላትን አሳትፎ እየሰራ ይገኛል። ከዚህ በኋላም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አባሉ አድርጎ እንደሚቀጥል ተገልጿል። ምክንያቱም የእርስ በእርስ መተጋገዝ ገንዘብን ብቻ ሳይሆን እውቀትንና ጉልበትን ያካትታል። በመሆኑም፣ በጎነትን የሚፈልግ ሁሉ ለተቸገሩ እንዲደርስበት የሚደረግበት አሰራር ነው መዘርጋት ያለበት። ማህበሩ በምንም መልኩ ከአንድ ሰው ተቀብሎ ወደ ሌላ ሰው ምግቡን እንዲያስተላልፍ አይፈልግም። ይህ የእሱ ስራ ይሆን ዘንድም አይሻም። ስለሆነም ዋና እቅዱ ሰዎችን ከሰዎች ጋር በማገናኘት እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ ማድረግ ነው። በሌላ በኩል ማህበሩ ጎዳና ላይ ያሉትን አይደግፍም። ምክንያቱም እዚያ እያሉ ማገዝ “ጎዳና ላይ መሆናችሁ ትክክል ነው፤ እዛው ጎዳና ላይ ቆዩ” ከማለት አይተናነስም። እናም የማህበሩ ዋና አላማ ከቤት ሳይወጡ የሚታገዙበትን ስርዓት መፍጠርና ለውጣቸውን እያዩ በእነርሱ ምትክ ሌላ ችግረኛ ሰው እንዲደገፍ ማድረግ ነው።

ማህበሩ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን፣ የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበርን፣ ከዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ (አብቹ ካንፓስ)ን ይዞ እየሰራ ያለ እንደሆነ ያጫወቱን አቶ ነጻነት፤ በእነርሱና መሰል አጋሮች እገዛ በሕግ ክልከላው መሰረት የአምስት ዓመት እቅዱን፤ ማለትም በኢትዮጵያ ውስጥ የጎዳና ላይ ልመናን ማስቆምን እውን እንደሚያደርግ ያምናል። ይህንን እውን ካደረገ በኋላ ደግሞ ራሱን ወደ ትምህርት ተቋምነት ለመቀየርም አስቧል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ዋና ግቡ መሰረቱን በመተጋገዝ ላይ ማጽናት ስለሆነ ነው። ከዚያ ማህበሩ ሥራውን ለማህበረሰቡ አስረክቦ፤ የትምህርት ማዕከል ሆኖ የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባሩን ይቀጥላል።

ማህበሩ አገርኛ ባህላችንን ይዞ ብቅ ማለቱና ለአብነት ያነሳናቸውን ባለታሪኮቻችንን እየፈጠረ በመሆኑ ይበል አሰኝቶናል። ይዟቸው እየተጓዘ ያሉት ሀሳቦች፤ ማለትም ‹‹ወላጆች በችግር ምክንያት ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ኃላፊነቴን እወጣለሁ፤ የተቸገሩ ጎረቤቶቼን በማገዝ ወደ ልመና እንዳይወጡ ኃላፊነቴን እወጣለሁ፤ በጎዳና ልመና ለተሰማሩ ወገኖቼ የመፍትሔ ባለቤት እሆናለሁ።›› የሚሉት የሁላችንም የቤት ስራዎች ናቸውና ልዩ ትኩረትን በመስጠት ሀላፊነታችንን እንወጣ ዘንድ በማሳሰብ ሀሳባችንን ቋጨን። ሰላም!!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ዘርፉን ለማዘመን የሚተጉ ወጣቶች

**አስናቀ ፀጋዬ**

የተገናኙት በስራ አጋጣሚ ነው። ሁለቱ በእንስሳት ህክምና ሳይንስ የተማሩ ሲሆን አንደኛው በጠፈር ምርምር አሜሪካን አገር ትምህርቱን ተከታትሏል። በዶሮ እርባታ በኩል ያለውን ክፍተት ለመሙላት በተለይ ደግሞ ዘርፉ በእውቀት የሚመራበትንና የሚሰራበትን መንገድ ለመፈለግ አንዳቸው ሀሳብ ጠንሳሽ ሌላቸው ሀሳብ ደጋፊና አብሮ የመስራት ፍላጎት በማሳየታቸው ወደ ዶሮ እርባታና እንቁላል ማስፈልፈል ስራ ገቡ።

በዚህም ተሳክቶላቸው የስጋ ዶሮዎችንና እንቁላል ለገበያ ማቅረብ ቻሉ። ቀስ እያሉ በዶሮ እርባታ፣ እንቁላል፣ በወተት ላም፣ በከብት እርባታና ማድለብ ስራ መሰማራት ለሚፈልጉ ወጣቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ከአዋጭነት ጥናት እስከ ምርት አቅርቦት ድረስ የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት አቋቋሙ።

ዛሬ ላይ ይህንኑ ስራቸውን አጠናክረው በቢሾፍቱ ከተማ የዶሮ ማርቢያ፣ እንቁላል ማስፈልፈያ፣ ከብት ማደለቢያና የላም ወተት ማምረቻ ማእከላት በተለያዩ ቦታዎች ከፍተዋል። ወደዚህ ስራ ለሚገቡ በርካታ ወጣቶችም ምርቶቹን በማቅረብና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ወደስራው እንዲቀላቀሉ አድርገዋል።

በዚህም በተለያየ መልኩ በራሳቸውና ከራሳቸው ውጪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር ችለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ የጀመሩትን ‹‹የሌማት ትሩፋት›› ፕሮጀክት በከተማ ደረጃ ለማሳካት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍም የበኩላቸውን አስተዋፆ እያደረጉ ይገኛሉ።

በቅርቡም አስፈላጊውን ጥናት በማካሄድ ‹‹የኢትዮጵያ ግብርና እንዴት ይዘምን?›› በሚል መሪ ሀሳብ በአዲስ አበባ ከተማ በአይነቱ የመጀመሪያና በርካታ ወጣቶችን የሚያሳትፍ ስልጠና ለማካሄድ እቅድ ይዘዋል። ይህም ወጣቱ በግብርናው ዘርፍ ገብቶ እንዲሰራና ዘርፉን በማዘመን ራሱን እንዲለውጥ እድል እንደሚሰጥ ተስፋ ጥለዋል የትረስት አግሮ ኮንሰልቲንግ መስራቾች።

ወጣት ዶክተር አቡኑ አንዳርጌ የትረስት አግሮ ኮንሰልቲንግ ዋና ስራ አስኪያጅ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪውን በእንስሳት ህክምና ከወለጋ ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። በተማረበት የትምህርት መስክ በዶሮ እርባታ ላይ በሚሰሩ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ ሰርቷል። በተለይ ደግሞ ከሰራባቸው ድርጅቶች በአንዱ ያየውን ክፍተት ስራውን እውቀት አክሎበት በራሱ እንዲሰራ አነሳስቶታል።

ከተመለከተው ክፍተት በመነሳት ሰዎች ትክክለኛ የዶሮ ምርቶችን ሳይንገላቱ እንዴት ማግኘት እንዳለባቸው ጥናት ማካሄድ ጀመረ። ሃሳቡ መሬት እንዲወርድና ግቡን እንዲመታ አቶ አሸናፊ ጌታሁን የተባለውና በአውስትራሊያ የሚኖረው ጓደኛው ድጋፍ ደግሞ ከፍተኛ ነበር። በስራ አጋጣሚ ቢሾፍቱ ከተማ የዶሮ መኖ በማቅረብ ያገኘው ሌላኛው ጓደኛው ዶክተር ተክሌ ሽፈራውም ስራውን ለመጀመርና አብሮ ለመስራት ያሳየው ፍላጎት የሚናቅ አልነበረም። የዶክተር አቡኑ ችግር ፈቺ ሀሳብ፣ ከጓደኞቹ የሃሳብ ድጋፍና አብሮ የመስራት ፍላጎት ጋር ተዳምሮ በዶሮ አቅርቦት በኩል የሚታየውን ችግር ሊፈታ የሚችል ‹‹ትረስት አግሮ›› የተሰኘ አማካሪ ድርጅት ፈጠረ።

ድርጅቱ ስራውን ሲጀምር በካፒታል ሳይሆን ሀሳብ በመፍጠር ነበር። ነገር ግን ጓደኛሞቹ ሃሳቡን ሲፈጥሩ ሃሳቡ እንዴት ገንዘብ ሊያመጣ እንደሚችል አስልተው ነበር ስራውን የጀመሩት። መነሻ ካፒታላቸውም 200 ሺ ብር ነበር። ይህም እቃ ግዢ፣ ቢሮ ማደራጀትና በማህበራዊ ሚዲያ ድርጅቱን ማስተዋወቅ ይጨምራል።

ድርጅቱ ስራውን በቢሾፍቱ ከተማ ሲጀምር በቅድሚያ የማማከሪያ ቢሮ ከፈተ። በመቀጠል ደግሞ በእንስሳት እርባታ ወጣቱና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እውቀትና ግንዛቤው ኖሯቸው ወደስራው እንዲገቡ በራሱ ማእከል ስልጠናዎችን መስጠት ጀመረ።

ስልጠናውን ከሰጠ በኋላ እውቀት ላይ የተመሰረተ የአዋጭነት ጥናት ወደ ዶሮ እርባታ ለሚገቡ ወጣቶች ሰራ። የቦታ መረጣም አደረገ። ስራውን በባለሞያዎች ካረጋገጠ በኋላ ዶሮ፣ የወተት ላም፣ ፍየል፣ በግ ከብትና የአሳ ማምርቶችን ጭምር የማቅረብ ስራዎችን አከናወነ።

ይህን ሁሉ ስራዎች ድርጅቱ ካከናወነ በኋላ በአምራቾችና ተጠቃሚዎች መካከል የገበያ ትስስር ይፈጥራል። ዶሮዎች እድሜያቸው ሲያልቅ/እንቁላል ጥለው ሲጨርሱና ወደ ስጋ ዶሮነት ሲቀየሩ/ድርጅቱ ተቀብሎ ይገዛቸውን መልሶ ለገበያ የሚቀርቡበትን አሰራር ዘርግቶ ወደ ህብረተሰቡ መግባት ችሏል። ይህንኑ ሰንሰለት በመፍጠር ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ወደስራ ገብቷል።

ገና ስራውን በጀመረ በአምስት ወራት ውስጥ ድርጅቱ ችግር ፈቺ ስራዎችን በመስራትና ህብረተሰቡም ስራውን ደስተኛ ሆኖ በመቀበል ስኬታማ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። በተለይ ማንኛውም በእንስሳት እርባታ ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ወጣቶችና ሌሎች የህብረሰተብ ክፍሎች ትክክለኛና በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ስራዎችን እንዲሰሩ ማድረግ ችሏል።

በአሁኑ ግዜ ትረስት አግሮ ኢንዱስትሪ ማንኛውም ወጣትና ሌላም ሰው እንስሳት አርቢ ወደ እርባታ ለመግባት ሲፈልግ አጠቃላይ ስልጠና እንዲሰጠው የማድረግ ስራዎችን ይሰራል። መኖ ማምረት ለሚፈልጉም ስልጣናዎችን ይሰጣል። ራሱ ድርጅቱ የመኖ ማሽኖችን ከውጪ አገር በማስመጣት ያስተክላል።

ወደስራው ለሚሰማሩ ወጣቶችና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች ለየትኛውም ባንክና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም የአዋጭነት ጥናት ሰርቶ ያቀርባል። ቦታ መረጣ አድርጎና የባለሙያ ድጋፍ አድርጎ ዶሮ፣ እንቁላል፣ የወተት ላም፣ በግ፣ ፍየልና ከብት በማቅረብ ወደ ሰዎች ስራ እንዲገቡ ያደርጋል።

ከዚህ ባለፈ ድርጅቱ በራሱ የሚያመርተው የዶሮ፣ እንቁላል በግ፣ ፍየል፣ ከብትና የወተት ላም ምርት አለው። ነገር ግን ድርጅቱ በራሱ በማምረት ብቻ የህብረተሰቡን ፍላጎት ማሟላት የማይችል በመሆኑ ከሌሎች ትላልቅ ድርጅቶች ጋር በመሆን ምርቱን ከነሱ ወስዶ ለህብረተሰቡ ያቀርባል። እንቁላል ከውጪ አገር በማስመጣትም የስጋ ዶሮዎችን በማስፈልፈል በራሱ ማእከል አማካኝነት ለተጠቃሚው ያቀርባል።

ድርጅቱ በማንኛውም የእንስሳት ልማት ዘርፍ መግባት ለሚፈልጉ ወጣቶችና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ከመሆኑ አኳያ ለአገልግሎት የሚጠይቀው ክፍያ አለ። ማንኛውም ወጣት ወይም ሌላ ሰው በእንስሳት እርባታ ዙሪያ የአንድ ሳምንት ስልጠና ለማግኘት 1 ሺ 500 ብር ይከፍላል።

ይህ እንዳለ ሆኖ አንድ ዶሮ አርቢ ገዝቶ ማርባት ከጀመረ በኋላ በአንድ ዶሮ በቀን ሁለት ብር እየከፈለ ሙሉ የክትባት፣ መንቁር ቆረጣና ሌሎችንም የጤና ክትትል አገልግሎቶች ያገኛል። በወተት ላም ላይም በወር በአንድ ላም ሁለት መቶ ብር በመክፈል ሁሉንም አይነት የክትትል አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል። ምርቱን ድርጅቱ የሚያቀርብ ከመሆኑ አኳያ እንደራሱ ምርት አድርጎ ይንከባከባል።

‹‹በዚህ የእንስሳት ልማት ዘርፍ በተለይ ደግሞ በዶሮ ላይ የሚሰሩት ስራዎች 99 ነጥብ 2 ከመቶ ያህሉ በእውቀት ላይ ተመስርቶ አይሰራም›› የሚለው ወጣት ዱክተር አቡኑ፤ ከዚህ ውስጥ 0 ነጥብ 8 ያህሉ ብቻ በዘመናዊ መልኩ እንደሚሰራበት ይናገራል። ይህም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የሚያመለክትና ድርጅቱም ዘርፉን በማዘመን ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ እንደሚገኝ ይጠቁማል።

የምግብ ዋስትና መረጋገጥ ስራዎች መሰራት ያለባቸው እንደ ትረስት አግሮ በመሰሉ አማካሪ ድርጅቶች መሆኑንም ተናግሮ፤ በተለይ ይህንን ከወጣቶች የስራ ፈጠራ ጋር አጣምሮ መስራት ከተቻለ ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር ያስችላል። ምርቶቹ ከአገር ውስጥ ፍላጎት በዘለለ ወደውጪ አገር የሚላክበት እድልም ስለሚፈጠር የውጪ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖራቸው ይጠቁማል።

ስራው የመንግስትን የልማት አቅጣጫንም ተከትሎ የሚከናወን ከመሆኑ አኳያና በተለይ ደግሞ የከተማ ግብርናን ከማስፋፋት አንፃር ፋይዳው የጎላ መሆኑንም ወጣት ዶክተር አቡኑ ይገልፃል። በይበልጥ ደግሞ ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር አብይ በቅርቡ ያስጀመሩትን የሌማት ትሩፋት የተሰኘ ፕሮጀክት በሚገባ የሚደግፍ መሆኑንም ይናገራል።

በቅርቡም ድርጅቱ እስከ 10 ሺ በአዲስ አበባና ዙሪያዋ የሚገኙ ወጣቶችን በማሰልጠን በእንስሳት ሃብት ልማት ዘርፍ ውስጥ ስራ ፈጥረው ራሳቸውን እንዲችሉ የሚያደርግ ፕሮጀክት ቀርፆ ‹‹ኢትዮጵያ መስራትና ስራ መፍጠር የሚችሉ ወጣቶችን ታፈራለች" የሚል ስኪል ኢትዮጵያ የተሰኘ ንቅናቄ በመመስረት ወደስራ መግባቱንም ነው የሚያብራራው። በዚሁ ስልጠና መክፈቻ ላይ ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዲገኙ ድርጅቱ በደብዳቤ ጥሪ መቅረቡንም ይገልፃሉ።

በስልሳ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ እንዲህ አይነት አደረጃጀት ያለው የማማከር ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳልተፈጠረና በዘርፉ የሚታየውን ክፍተት በማየት ድርጅቱ ወደስራ መግባቱንም ያስረዳል። ከተለመደው አሰራር ወጣ በማለት ድርጅቱ ህብረተሰቡን የማገዝ ስራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝም ወጣት ዶክተር አቡኑ ይጠቁማል።

እስካሁን ባለው ሂደት ድርጅቱ ከተለያዩ ትላልቅ ድርጅቶች ጋር ሰርቷል። ከጠቅላይ ሚንስትር ቢሮም ጋር አንዳንድ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። አሁንም የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ የህብረት ስራ ባንኮች፣ ሌሎች ግለሰቦችና ባለሃብቶች የድርጅቱን ሃሳብ በመያዝ በጋራ ቢሰሩ ለህብረተሰቡ የተሻሉ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ስራዎችን ማከናወን እንደሚቻል ያምናል።

በቀጣይም ድርጅቱ በርካታ ስራዎችን ለማከናወን የተለያዩ እቅዶችን ይዟል። ለአብነትም ከተለመደውን የዶሮ ማርባትና እንስሳት ማደለብ በመውጣት አሰራሩን ይበልጥ የማዘመን ስራ ለመስራት አቅዷል። 100 ሺ ለሚሆኑ ወጣቶች እንዴት ስልጠና መስጠትና እውቀት ላይ የተመሰረቱ ስራዎችን መስራት እንደሚቻል ብሎም ህብረተሰቡ በእንስሳት ሀብት የምግብ ዋስትናውን በምን መልኩ ማረጋገጥ እንዳለበት አበክሮ ይሰራል።

በቅርቡ ደግሞ 10 ሺ የሚሆኑ ወጣቶችን ለማሰልጠን የሚያስችል ንቅናቄ በአዲስ አበባ ለማካሄድ ውጥን ይዟል። ይህም በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያዋ ያሉ ወጣቶች ገንዘብ ሳይኖራቸው ወይም በአነስተኛ ገንዘብ በአጭር ግዜ ውስጥ በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችል ስራ እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል። ይህም ወጣቱ ስራ እንዲኖረው የሚያደርግ በመሆኑ በአገሪቱ ሰላም እንዲረጋገጥ ያደርጋል።

የድርጅቱ አብዛኛዎቹ ደምበኞች በአዲስ አበባ ከተማ እንደመሆናቸው በከተማዋ ትልቅ የምርት ማእከል በመክፈት ደምበኞቹን ተደራሽ የማድረግ ውጥንም ይዟል። እስካሁን ባለው ሂደትም በድርጅቱ ውስጥ ለሚሰሩ 11 ሰራተኞች ቋሚ የስራ እድል ተፈጥሯል። ከዚህ ውጪ በዚሁ ስራ ማለትም በጫኝና አውራጅ፣ ምርት ለማጓጓዣ በመኪና ኪራይ አቅርቦትና በሌሎችም የቀን ገቢ ለሚተዳደሩ በርካታ ወጣቶች በተዘዋዋሪ የስራ እድል ተፈጥሯል። ሌሎች በርካታ ወጣቶችም ከድርጅቱ የምክር አገልግሎት አግኝተውና ምርት ተቀብለው የራሳቸውን ስራ መፍጠር ችለዋል።

ወጣቶች ሩቅ ያለውን ሳይሆን ራሳቸው ጋር ያለውን ነገር መመልከት ከቻሉ በርካታ ነገሮችን መፍጠር እንደሚችሉ የሚናገረው ወጣት ዶክተር አቡኑ፤ በአሁኑ ግዜ ዋጋ ስለማይሰጠው ነው እንጂ ከዚህ በፊት ብዙዎች ትምህርት የሚወስዱት በግብርናውና በእንስሳት ሀብት ዘርፍ ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉ ይናገራል።

አሁንም ቢሆን ግብርናው በቴክኖሎጂ ተደግፎ እየተሰራበት ባለመሆኑና ሰፊ የሚሰሩበት መስኮችን ያቀፈ በመሆኑ ወጣቱ በእንስሳት ሀብት ልማት ብቻ በመሳተፍ ራሱንና አገሩን ሊለውጥ የሚችልበት እድል እንዳለ ይጠቁማል። ከዚህ ባለፈ የራሱንና የሌሎችንም የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ እንደሚችልም ይጠቅሳል። ከዚህ አኳያ ወጣቱ ሳያመነታ በዚህ ዘርፍ በመግባት ራሱንና አገሩን መለወጥ አለበት ሲል መልእክቱን ያስተላልፋል።



ከግራ ወደቀኝ ዶክተር ተክሴ ሽፈራው እና ዶክተር አቡኑ አንዳርጌ፤

# በአማራ ክልል ለአካባቢ የማዕድን ሀብት ልዩታ የተሰጠ ትኩረት

**ስምስም መንግሥቱ**

በኪነህንፃ ውበታቸውና ሰማይ ጠቀስ ሆነው በመገንባታቸው አድናቆት የሚቸራቸው፣የአንዳንድ አገራት ህንፃዎች የጥበበኛው እጅ ውጤቶች መሆናቸው ቢታወቅም፤ ለግንባታ የዋለው ግብአትም ለውበታቸው ወሳኝ እንደሆነ በምክንያትነት ይጠቀሳል። የህንፃው ምሶሶ፣ጣሪያና ግድግዳው፣ ማጠናቀቂያው በአጠቃላይ ጥቅም ላይ የሚውለው አብዛኛው የግንባታ ግብአት ከምድር ውስጥ የተገኘ የማዕድን ሀብት ውጤት ነው።

እንደ ሴራሚክ፣ ለደረጃ፣ ለወለልና ለመሳሰሉት የሚውለው እብነ በረድና ሌሎችም የህንፃው ማጠናቀቂያ ግብአቶች የተለያየ ህብረቀለም ያላቸው በመሆኑ የህንፃውን ውበት ከፍ ያደርጉታል። ለተፈጥሮ ሀብት ያለው አድናቆት እንዲጨምርም ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ በተለይም በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ከተሞች በጭቃ እና በእንጨት የሚከናወኑ ግንባታዎች በዘመናዊ የግንባታ ግብአቶች መተካት ከጀመሩ ወዲህ የምድር ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት የሆነው ማዕድን ጥቅምና አስፈላጊነቱ እየጎላ መጥቷል።

ለማጓጓዣ ዘርፉ ጥቅም እየሰጠ ያለውና ለአንድ አገር ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ተደርጎ የሚወሰደው ነዳጅም እንዲሁ የምድር ውስጥ ፀጋ ነው። የተፈጥሮ የነዳጅ ሀብታቸውን በመጠቀም የበለፀጉ አገራት በርካታ ናቸው። በዋጋ መናር የአገሪቱን የኢኮኖሚ አቅም በእጅጉ እየተፈታተነ ያለውን ከውጭ የሚመጣውን ነዳጅ ማስቀረት የሚቻለው አገር ውስጥ አለ የሚባለውን የምድር ውስጥ ሀብት/ ነዳጅ/ ጥቅም ላይ ማዋል ሲቻል ብቻ ነው።

የማዕድን ዘርፉ ለጌጣጌጥና መዋቢያዎች ጭምር የሚውል ሀብት በመሆኑ አገልግሎቱና የሚያስገኘው ጥቅም ዘርፍ ብዙ ነው። በብዙ ድካም በቁፋሮ ከምድር ውስጥ ወጥቶ እሴት ተጨምሮበት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው የምድር ውስጥ ሀብት የሆነው ማዕድን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍ እያለ በመምጣቱ የመንግሥታትም የትኩረት አቅጣጫ ሆኗል።

ነዳጅ፣ ወርቅና ለጌጣጌጥ እንዲሁም ለኢንዱስትሪና ለግንባታው ዘርፎች ግብአት የሚሆኑ እምቅ የማዕድን ሀብቶች በስፋት እንዳላት የሚነገርላት ኢትዮጵያም በዘርፉ ኢንቨስትመንት በመሳብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቷን ለማሳደግ በተለይም አገራዊ ለውጥ ከተደረገ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በዘርፉ ሲደረግ የነበረው እንቅስቃሴ ተጠናክሯል። በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው (ሪፎርም) በአገር ኢኮኖሚ ላይ እድገት ለማስመዝገብ ወሳኝ ናቸው ተብለው ከተመረጡ አምስት የትኩረት አቅጣጫ ዘርፎች አንዱ ማዕድን ተደርጓል።

በዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ውጤት ለማስመዝገብም ኢንቨስትመንትን መሳብ ይጠበቃል። ለእዚህ ደግሞ በመጠንና በአይነት በየትኛው የአገሪቱ አካባቢ ሀብቱ እንደሚገኝ በጥናት ታግዞ በተደራጀ ሁኔታ ሀብትን በመለየት ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ በዩኒቨርሲቲዎችና ዘርፉን በሚመራው ተቋም የጥናትና ምርምር ሥራዎች መሰራታቸው ይታወሳል። ሆኖም ግን አጥጋቢ እንዳልሆነና ሥራዎች እንደሚቀሩ ይነገራል።

በጥናት የተለየውንም ሀብት በማስተዋወቅ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የተደረገው ጥረት አነስተኛ እንደሆነም ይተቻል። በሌላ በኩልም ሀብቱ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ያለው የተቋም አደረጃጀትና በባለሙያዎች የታገዘ ሥራ በመሥራት ረገድም ክፍተት መኖሩ ይነሳል።የተጠናከረ አደረጃጀት ሲኖር በዘርፉ ለመሰማራት ለሚፈልግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል። ለማእድን የተሰጠውን ትኩረት ተከትሎ የአደረጃጀት ለውጦች ቢደረጉም፣ አሁንም ዘርፉን የሚመራው የቢሮ አደረጃጀት ትኩረት እየሰጠ ያለው ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢ ላይ አለመሆኑ እየተጠቆመ ይገኛል። ዘርፉ ከሌላ የሥራ ክፍል ጋር እንዲመራ መደረጉና በአንዳንድ የማዕድን መገኛ አካባቢዎች በጽህፈት ቤት ደረጃ የተደራጀ መሆኑ ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ እንደሆነ በማሳያነት ይጠቀሳል። እንዲህ ያለውን አሰራርም መፈተሽ ይገባል የሚል ሀሳብ በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች አስተያየት ይሰጣል።

> **የማዕድን አይነቱንና ክምችቱን ማረጋገጥ የሚቻለው በቤተሙከራ በመሆኑ ማስመርመሩ ወሳኝ ነው። እንዲህ ባለ መንገድ ነው ከትንሽ ወደ ትልቅ ሥነምህዳር ካርታ ማሳደግና ሥራውንም አገራዊ ማድረግ የሚቻለው። አሁን ዘመኑ የሚጠይቀው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመሆኑ ከጊዜው ጋር መሄድ ግድ ይላል**

በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለይቶ ለለውጥ መነሳሳት እየተፈጠረ ባለበት በዚህ ወቅት በአካባቢያቸው ያለውን የማዕድን ሀብት በአይነትና በመጠን ለይቶ ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ ጥረት በማድረግ ላይ ከሚገኙት ክልሎች መካከል የአማራ ክልል ይጠቀሳል። ክልሉ ከፍተኛ የማዕድን ክምችት ከሚገኝባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች መካከልም አንዱ መሆኑ ይነገራል። በዋጋ ውድ የሆነና በዓለም ገበያ ተፈላጊ ከሆኑት የጌጣጌጥ ማዕድናት መካከል ኦፓል ማዕድን በክልሉ ወሎ አካባቢ በስፋት እንደሚገኝ፣ በአጠቃላይ የዓባይ ሸለቆን እና በሰሜን ሸዋ ዞን የጀማ ተፋሰስን ተከትሎ ባሉ አካባቢዎች ለኢንዱስትሪና ለግንባታ ዘርፎች ግብአት የሚውሉ ከፍተኛ ክምችት ያላቸው የማዕድን ሀብቶች መኖራቸውን የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲን ዋቢ አድርጎ መረጃውን ካሰራጨው አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን (አሚኮ) ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በክልሉ ከፍተኛ የማዕድን ክምችት ቢኖርም ከዕውቀት እና ክህሎት እጥረት እንዲሁም ከትኩረት ማነስ ጋር በተያያዘ ክልሉ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም አለማግኘቱም በመረጃው ተጠቅሷል። በክልሉ ብቻ ሳይሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ሊያሠራ የሚችል ግልጽና አስተማማኝ ፖሊሲ እና ስትራቴጅ ተቀርፆ አለመተግበሩም ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱ ተመልክቷል።

ክልሉ ቀድሞ የነበሩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመሙላትና ያለውንም ሀብት በጥናት ለይቶ ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ በዚህ ወቅት እንደ አገር ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረትና በዘርፉ የተደረገውን የፖሊሲ ማሻሻያ መሠረት በማድረግ በለውጥ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። በተለይም በክልሉ የሚገኘውን ሀብት በአይነትና በመጠን ለይቶ በተደራጀ ሁኔታ ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ የክልሉ ማዕድንና ሀብት ልማት ኤጀንሲ በራሱ አቅም ካካሄዳቸው የጥናት ሥራዎች በተጨማሪ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ሰርቬይንግ ጨምሮ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ሌሎችም የትምህርት ተቋማት ባካሄዱት ጥናት በአምስት ዘርፎች የተከፈሉ 40 ያህል የማዕድን አይነቶችን ለይቶ ዝግጁ ማድረጉንና በጥናት ለይቶ ያደራጃቸውን የማዕድን አይነቶች በቅርቡ በክልሉ ባካሄደው የማስተዋወቂያ መርሃግብር ላይ ለማስተዋወቅና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ያደረገው ጥረት ይታወሳል።

ኤጀንሲው በዘርፉ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ በክልሉ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲያግዙት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ሰሞኑን ከአምስት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል። ዩኒቨርሲቲዎቹም በስምምነቱ መሰረት ለመስራት ዝግጁነታቸውን ገልጸዋል።

በመግባቢያ ሰነድ ስምምነቱ ዙሪያ ያነጋገርናቸው የክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ኤጀንሲ ኃላፊ አቶ ኃይሌ አበበ እንዳስረዱት፤ በማዕድን ዙሪያ በተዘጋጀ መድረክ ከትምህርት ተቋማቱ ጋር ውይይት ከተደረገ በኋላ ነው የጥናትና ምርምር የመግባቢያ ሰነዱ የተፈረመው።የማዕድን ሀብት ልየታና ግመታ መሠረት ባደረገ ነው የጥናት ሥራው የሚከናወነው።

በክልሉ በማእድን ሀብቱ ላይ የጥናት ሥራዎችን ማከናወን አዲስ እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ ከዚህ ቀደም በሥነምድር ወይም ካርታ (ማፐ) ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት መካሄዱን ተናግረዋል። የዚህ ጥናት ወሰኑ (ካሬ ሜትር) አነስተኛ መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

የዚህኛውን የጥናት ሥራ ለየት የሚያደርገው፤ ጥናቱ በቅርብ ርቀት በሚገኙ ወረዳዎች ላይ ትኩረት ያደረገና ጥናቱ የሚሸፍነውም የካሬ ሜትሩ ስፋት ከፍ ይላል። በዚሁ መሠረትም 6ሺ742ካሬ ኪሎ ሜትር አካበቢ ነው የሚሸፍነው። ጥናቱ በክልሉ የሚገኘውን የማዕድን መጠንና ክምችትን ያካተተ መሆኑም የተለየ ያደርገዋል።

ኃላፊው እንዳሉት፤ ጥናቱን የሚያካሂዱት ዩኒቨርሲቲዎች ጂኦ ኬሚስትሪና ጂኦ ፊዚክስ የሚባለውን በመለየት በቤተ ሙከራ (ላብራቶሪ) የተረጋገጠ ሥራ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል። ስምምነቱ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሥራ በመግባት ግንቦት ወር 2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የጥናት ሥራው መጠናቀቅ ይኖርበታል።

በክልሉ በሚገኙ አምስት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ሰሜሸዋ አንኮበር፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ አምባሰል ወረዳ፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ መተማ ቋራ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ምዕራብ ጎጃም አካባቢዎች እንዲሁም ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ በዙሪያው ትኩረት በማድረግ ጥናቱን ያካሂዳሉ።

የጥናት ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቅሰው፣ ሰሞኑን ጎንደር ላይ ለተመሳሳይ ሥራ ከአስር ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ለማድረግ እቅድ መያዙን አቶ ኃይሌ ገልጸዋል።

የጥናት ሥራው ዋና ተልእኮ በቤተሙከራ የተረጋገጠ የጥናት ሥራ በማከናወን በክልሉ ያለውን የማእድን ሀብት በመጠን እንዲሁም ሀብቱ የሚገኝባቸውን አካባቢዎች ለይቶ ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ መሆኑንም አመልክተዋል። ከሀብት ልየታው በኋላ ወደ ልማቱ ሥራ ለመግባት ስላለው ቁርጠኝነት አቶ ኃይሌ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ከዚህ ቀደም በጥናት የተለዩትን ወደ ሥራ በማስገባት የተሰሩ ሥራዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ አሁንም ይሄው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በገባው የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መሠረት ጥናቱን በወቅቱ አጠናቅቆ ለማስረከብ ሥራ መጀመሩን በጥናቱ ዙሪያ ያነጋገርናቸው የዩኒቨርሲቲው ተባባሪ ፕሮፌሰርና የጥናት ቡድኑ ኃላፊ ዶክተር ዳዊት ለበኔ ገልጸውልናል። እንደ ዶክተር ዳዊት ገለጻ፤ የጥናቱን ሥራ የሚያከናውኑትን አምስቱን ዩኒቨርሲቲዎች ጎንደርና ባህርዳር ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው የሚመሩት።

ዩኒቨርሲቲዎቹም ለጥናት ሥራው ግማሽ የሚሆን በጀት በማዋጣት ተሳታፊ እንዲሆኑ ነው የተደረገው። የጥናት ሥራውንም የሚያከናውኑት በቅርብ አካባቢ ነው። ስምምነቱ የማዕድን አይነቱን ለመለየትና መጠኑንም ለማወቅ በመሆኑ ለዚህም ዝግጅት ተደርጓል። በጥናት ሥራው ማዕድኖቹ የሚገኙባቸውን አካባቢዎች በቀላሉ ለማወቅ እንዲቻል የሥነምድር ካርታ (ማፐ) ሥራ ይቀድማል። ማዕድኑ መኖሩ ከተረጋገጠ የማዕድኑ የአለት ናሙና በቤተሙከራ ይመረመራል። የጥናት ሥራው የሚጠናቀቀው ይህን ሁሉ ሂደት አልፎ ነው።

የጥናት ሥራውን በዘመናዊ ቤተሙከራ የታገዘ ለማድረግ አቅም ስለመኖሩ ዶክተር ዳዊት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የአቅም ጉዳይ አንዱ ክፍተት መሆኑን ተናግረዋል። የስምምነት ሰነዱ ከመፈረሙ በፊትም በውይይት ላይ የተነሳ ጉዳይ እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን ባለው ሁኔታ የተሻለ ተሞክሮ ያለው አገር ተመርጦ የአለት ናሙናውን በመላክ የመመርመሩን ሥራ ለማከናወን መታሰቡን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የማዕድን አይነቱንና ክምችቱን ማረጋገጥ የሚቻለው በቤተሙከራ በመሆኑ ማስመርመሩ ወሳኝ ነው። እንዲህ ባለ መንገድ ነው ከትንሽ ወደ ትልቅ ሥነምህዳር ካርታ ማሳደግና ሥራውንም አገራዊ ማድረግ የሚቻለው። አሁን ዘመኑ የሚጠይቀው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመሆኑ ከጊዜው ጋር መሄድ ግድ ይላል።

ቤተሙከራውን በአገሪቱ ለማቋቋም አቅም ይጠይቃል። በሂደት ግን ማቋቋሙ የግድ ይሆናል፤ ሀሳቡም አለ ሲሉ ጠቁመዋል።

የጥናት ሥራው ውጭ አገር ድረስ በመላክ የሚከናወን በመሆኑ ከፍተኛ በጀት ይጠይቃል። ከዚህ አኳያ ስለተደረገው ዝግጅትም ዶክተር ዳዊት እንዳብራሩት፤ ሥራው ከፌዴራል ወደ ክልል የወረደ መሆኑንና ጠንክሮ መሥራትን እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፣ ከዚሁ አኳያ ጥረት እየተደረገ እንደሆነም ነው የማውቀው ሲሉ ገልጸዋል።

በጥናት የተገኘውን ውጤት ወደተግባር መቀየር ሲቻል ነው የማዕድን ዘርፉ በኢኮኖሚ ላይ ያለውን አበርክቶ ማረጋገጥ የሚቻለው። ተደጋግሞ እንደሚባለው የጥናት ሥራዎች ወደተግባር አይለወጡም። እንዲህ ያለው ክፍተት አሁን በተጀመረው የጥናት ሥራ ላይም በተመሳሳይ እንዳያጋጥም ምን መደረግ እንዳለበትም ዶክተር ዳዊት ምክረሀሳብ ጠይቀናቸው ‹‹ትክክል ነው፤ ለአብነት ከዚህ ቀደም ቋራ ላይ በሥነምድር ካርታ ከ50 እስከ 60 በመቶ የሚሆን ብረት ማግኘቱን ለሚመለከተው አካል አሳውቀናል። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ለግንባታና ለኢንዱስትሪው ግብአት የሚሆኑ ማዕድናትን በምርምር ለይቶ ለሚመለከተው አካል የጥናት ውጤቱን ሰጥቷል። ይህ ሁሉ ግን ወደተግባር መቀየሩን አላወቅንም።ተመራማሪው ከማሳየት በላይ መሄድ አይችልም ሲሉ አብራርተዋል።

ዘርፉን የሚመራው አካል ግን ተከታትሎ ለሥራ እንዲውል ማድረግ እንደሚጠበቅበት አስታውቀው፣ የውጭ ኢንቨስተርን ከመሳብ ጎን ለጎን ወጣቶችን በማደራጀት ወደ ሥራ ማስገባት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል። ዘርፉን የሚመሩት በየጊዜው መቀያየር የጥናት ሥራዎች ወደተግባር እንዳይቀየሩ አንዱ እንቅፋት እንደሆነም ነው ያመለከቱት።

የክልሉ ማእድን ልማት ኤጄንሲ በማእድን ሀብት ላይ ጥናት በማድረግ ለባለሀብቶችና ለሌሎች አልሚዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እያከናወነ ያለው ጥረት አርአያነት ያለው ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ሌሎች ክልሎችም ከዚህ መማር ይጠበቅባቸዋል። ክልሉ በጥናቱ ይህን ያህል ርቀት እንደ ሆነ ሁሉ ጥናቱ መሬት ላይ ወርዶ ክልሉንም አገሪቱንም ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችልበት ሁኔታ ላይ በትኩረት መስራት ይኖርበታል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## አመልና ፍቅር

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ልማድ አለብኝ ክፉ ልማድ..ጥፍሬን እበላለው፣ ጸጉሬን እቆነድዳለው። እኚህ ልማዶቼ በሰው ፊት አላሳነሱኝም። አንዳንድ ጊዜ እናቴ ‹እጅህን ከራስህ ላይ አውርድ ብላ በማማሳያ ከመማታቷና ጥፍርህን ለምንድነው የምትበላው? ከማለት ባለፈ ያን ያክል ሰው አፍ ላይ አልጣለኝም። ከሁሉም የከፋው ልማዴ አስራ ስምንት ዓመት የልደት ቀኔን ተከትሎ የመጣው ልማዴ ነው። እንዴት እንደተለማመድኩት ሳላውቀው እጆቼ አፍንጫዬን አፍቅረው አገኘኋቸው። አፍንጫዬን ሳልጎረጉር፣ የደረቀና ትኩስ ንፍጥ በጣቴ ይዤ ሳልወጣና ሳላፍተለትል ቀርቼ አላውቅም። ሌባ ጣቴን አፍንጫዬ ላይ ጣል አድርጌ በአውራ ጣቴ እገዛ ከገዛ ንፍጤ ጋር እጫወታለው። በመድረቅና በመርጠብ መካከል ያለ ወፍራም ዳለቻ ንፍጥ መንግዬ በአውራ ጣቴና በሌባ ጣቴ መሀል አድርጌ አድበለብለዋለው።

ሌላው አልተው ያለኝ ልማዴ..የሰውነቴን ቆሻሻ ቦታ በጣቶቼ የመፈለግ አባዜ ነው። ህይወት የውበቷን ያክል ቆሻሻም አላት እላለው። አንዳንድ ጊዜ ሰውነት የቆሻሻ እቃ ቤት ነው..የጉድፎች መከማቻ። እስኪ ራሳችሁን ተመልከቱት..የቆሸሸና ለመንካት የሚያስነውር የሰውነት ክፍል የላችሁም? ስትነኩት የሚሰነፍጥ፣ በውሀና በሳሙና ታጥበነው የማይጸዳ ጉድፍ በሰውነታችን የሆነ ቦታ ላይ የለም? በደንብ አለ..ከዛ ነገር ጋር ነው ፍቅር የያዘኝ። በዛ ነገር ነው ፍቅር የወደኩት። የትም እንዴትም ልሁን እጆቼ አፍንጫዬን ሳይጎረጉሩ፣ ብብቴን ሳይቧጥጡ አይውሉም። አጠገቤ የተቀመጡ ሰዎች በድርጊቴ ምን ያክል እንደሚጸየፉኝ ለማሰብ ጊዜ አጥቼ ከነውሬ ጋር እነውራለው። እጆቼን ብብቴ ውስጥ አስገብቼ በላብና በጠረን የሻገተ አመዳይ ጸጉሬን አርመጠምጣለው። አርመጥምጬ አላበቃው ከገላዬ ውስጥ እጄን መዝዬ ወደ አፍንጫዬ ሰድጄ አሸተዋለው። ያኔ አጠገቤ ያለው ሰው የሚሆነው መሆን አይታሰበኝም። በቃ ለአስቀያሚ ልማዴ እጅ የሰጠሁ ነኝ። በዚህ ባበቃ ጥሩ ነበር..ግን አላበቃም..እጄ የማይሄድበት ቆሻሻ ቦታ የለም። ቦላሌዬን አልፎ፣ ቡታንታዬን አልፎ ጉድፍ ካለበት ቦታ መሄድ ያምረዋል። እዛም አደብ አይገዛም..ከሰውነቴ የቆሻሻ ገንዳ ከመቀመጫዬ ስፍራ ሲያውደለድል አገኘዋለው። ብብቴን፣ አፍንጫዬን፣ ጸጉሬን፣ ቂጤንና ጉያዬን በነካሁበት እጄ ለማዕድ እቀርባለው። ይሄን ነኝ እኔ..

እናቴ ይሄን ልማዴን ለማስተው ያልፈነቀለችው ድንጋይ የለም። ‹ከለማበት የተጋባበት አሉ..ከየትኛው ባለጌ ወዳጅህ ጋር እየዋልክ ነው እንዲህ ነውረኛ የሆንከው? ትለኛለች..የቡና ስኒዋን እያጠበች። የቡና ስኒዋን እያጠበች ብቻ አይደለም ቡና ስትቆላም ሆነ፣ ስትቀዳ እንዲህ ሳትለኝ ቀርቼ አላውቅም። እናቴ አጠገብ ካለሁ እኔም አፍንጫዬን ከመጎርጎር እሷም እኔን ከመቆጣት አትቆጠብም። ሳላስበው እጄን አፍንጫዬ ላይ አገኘዋለሁ አፍንጫዬን እየጎረጎርኩ እንደሆነ የማውቀው በእናቴ ቁጣ ነው። ‹ባለጌን ካሳደገ የገደለ ይጸድቃል..› ትለኛለች በምሬት።

**“እኔ ባለጌ ነኝ? እላታለው።**

**“ለዛውም የወጣለት ባለጌ ነዋ! ስትል ድምጽዋን ጫን አድርጋ ትመልስልኛለች።**

**“ታዲያ ለምን ገለሽኝ አትጸድቂም? ስል ለመቀለድ እሞክራለው።**

**“ወልጄ፣ ገድዬ እንዴት እችለዋለው? እሷው የፈረደባት ትቃጠል‹ ትለኛለች።**

**በነገር እየወጋችኝ እንደሆነ አላጣሁትም። ቀጠል አድርጋ €በዚህ አመልህ የትኛዋ ሴት ይሆን የምታገባህ? አለችኝ።**

**“ማን እኔ ነብዩ ነኝ ሴት የማጣው.. ካላግበሰበስኩልሽ ምናለ ትደኛለሽ‹ ስል ጎራ ይነፋኛል።**

**“ማግበስበስ ቁም ነገር አይደለም አንዲትን ሴት ሚስት ማድረግ ነው ቁም ነገሩ‹ ስትል ልታርመኝ ትሞክራለች።**

**“አይ ሴት..! ስትል በዝምታ ትወድቃለች።**

**“ምነው? ስል ከሀሳቧ እመልሳታለው።**

**“ሴትነት ገርሞኝ ነው..‹ ትለኛለች።**

**“ለምንድነው ሴት ሆነሽ ሴትነት የሚገርምሽ?**

”እንዴት አይግረመኝ! ሴት የወንድ ልጅ የጉድፉ እቃ ቤት ናት። ስንቱን ችላ፣ ስንቱን አጥርታ የምትኖር። አባትህን ሳገባው እንዳሁኑ አልነበረም። ለካራምና ዘማዊ፣ ሀይለኛና ተደባዳቢ ነበር። እኔን ካገባ በኋላ ነው ሰው የሆነው። ነፍሴ ነች የፈጠረችው..በባዶነቱ ውስጥ ገብቼ ነው ዛሬን የሰጠሁት። በእያንዳንዷ ሴት ልብ ውስጥ ብዙ ያላለቁ ወንዶች አሉ። ወንዶች በሴት ልብ ውስጥ ነው እድገታቸውን የሚጨርሱት›። ብላ ዝም አለች። ከዚህ ንግግሯ በኋላ ዝምታዋ ተከተለ።

በአንድ ግዜ ምን ነካት እያልኩ ሳስብ ለካ ስሰማት የነበረው እጄን አፍንጫዬ ላይ ሰቅዬ ነበር።

‹ሴት የሌለችበት የወንድ ስፍራ የለም። ሴት መቼም ሙሉ ናት። ወንድ ሙሉ የሚሆነው ከሴት ጎን ሲቆም ነው› ብላኝ ትታኝ ወደ ውጪ ወጣች።

ጊዜአት ነጎዱ..እኔና አመሌ ግን አልተለያየንም። እውነት ለመናገር ልማዴን ለማሸነፍ ያላደረኩት ጥረት የለም። ግን በቃ አቅም አጣሁ..። ስራ ሳጣ መሄጃዬ ወደ ልማዴ ነው። ስተክዝ አፍንጫዬን እየጎረጎርኩ ነው። ስደሰት እጄን ብብቴ ውስጥ አስገብቼ ነው። በዚህ ልማዴ ውስጥ እያለሁ የምሰራበት መስሪያ ቤት አዲስ ከገባች ሴት ጋር ተዋወኩ። ገና እንዳየኋት ነው ስብርብር ያልኩላት። ሳናግራት እንዴት ሆኜ እንደነበር አላስታውስም..ብቻ እጄን አፍንጫዬ ላይ ሰቅዬ እንዳይሆን መድሀኒዓለምን እለምነዋለው። ያለቦታዬና ያለስራ መደቤ ወዳለችበት እየተመላለስኩ በድርቅና ተወዳጀኋት። እሷን ለማየት ስል ሳምንቱን ሙሉ ስራ ብገባ፣ ሳምንቱን ሙሉ ስራ ቢኖር ስል ተመኘሁ።

በጣም ተቀራረብን..እንዳላጣት መፍራት ጀመርኩ። በጣም ስቀርባት ምን እንደምላት እየጠፋኝ መጣ። ቤዛ ፊት ስቆም እናቴ ናት ትዝ የምትለኝ። ለእናቴ የጎረርኩት ብዙ ጉራ አለ..አመሌን ተንተርሳ ‹በዚህ ልማድህ የትኛዋ ሴት ይሆን ባል የምታደርግህ? ስትለኝ ‹ማን እኔ ነብዩ ነኝ ሚስት የማጣው?..ከፈለግሽ አግበሰብስልሻለው› ብያት አውቃለው። አሁን ላይ ያ ሁሉ ድፍረቴ ከዳኝ። ሴት ለማግበስበስ አይደለም ለቤዛ የሚሆን ወኔ እየከዳኝ መጣ። ሚስት ማግኘት እንዴት መከራ እንደሆነ በቤዛ ነው ያወኩት። በተለይ ለእንደኔ አይነቱ በብዙ ልማድ ለሚኖር ሰው ሁነኛ ሴት ማግኘት አዳጋች ነው። ሴቶቻችን ጥሩ የለበሰና እንከን አልባ ወንድ በሚፈልጉበት በዚህ ዘመን እጄን አፍንጫና ብብቴ ውስጥ እየቀረቀርኩ የትኛዋ ሴት ናት ባል የምታደርገኝ እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ። እናቴ እውነቷን ነው ወንድ ልጅ የሚጸዳው..ወንድ ልጅ የሚጠራው በሴት ነው።

ከቤዛ ጋር ልንገናኝ ተቀጣጠርን..ወኔ ከድቶኝ ፊቷ ስቀርብ እንዴት መሆን እንዳለብኝ ለማወቅ ስል ስለሴት የተጻፉ መጽሀፎችን አገላብጥ ጀመር። ሴቶች የሚጠሉት የወንድ አይነት በሚል ርዕስ ስር እንዲህ ተጽፎ አነበብኩ..‹ሴቶች ንጽህናውን የማይጠብቅ ወንድ አይወዱም› የሚል። በትንሹ እኔን የሚነካ መሰለኝ። ቀጥዬ ባነበብኩት ርዕስ ስር ግን እንዳለ ራሴን አገኘሁት። ‹ሴቶች የሚጠሉት የወንድ አይነት በሚል ሌላ ርዕስ ስር ከተጻፉ አስር ነውሮች ውስጥ ሰባቱ የኔ አመሎች ነበሩ።

ከቤዛ ጋር ተገናኘን..ያን ቀን እጄን ወደ አፍንጫዬ.. ወደ ብብቴ ላለመስደድ የለፋሁትን ልፋት ለምንም ለፍቼው አላውቅም። ሚስት ማግኘት እንዴት መከራ ነው የሚል እንጉርጉሮ ሳንጎራጉር ነበር።

# ዓለም አቀፍ

## በደቡብ ሱዳን በተቀሰቀሰ ግጭት ከ166 ሰዎች በላይ ተገደሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ሱዳን በተቀሰቀሰ ግጭት ከ166 ሰዎች በላይ ሲገደሉ ከ20ሺህ ዜጎች በላይ ከቀዬአቸው መፈናቀላቸውን ቢቢሲ አስነበበ።

በደቡብ ሱዳን የላይኛው ናይል ግዛት በተቀሰቀሰው ግጭት 166 ንጹሀን ዜጎች መሞታቸውን፣ ከ3 ሺህ በላይ ዜጎች ወደ ሱዳን መሰደዳቸውን እና ከ20 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች መፈናቀላቸውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር አስታውቋል።

የድርጅቱ ኃላፊ ቮልከር ቱርክ በሰጡት መግለጫ፣ “እነዚህ ከስርዓተ ጾታ ጋር የተዛመዱ ጥቃቶች፣ አፈናዎች፣ የንብረት ውድመት እና ዘረፋ የተያያዙ ግድያዎች ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ረገጣ እና ወንጀሎች ናቸው እናም መቆም አለባቸው” ብለዋል።

የአካባቢው ባለስልጣናት እና የማህበረሰብ መሪዎች ትጥቅ ባነገቡ ቡድኖቹ መካከል ያለውን ውጥረት ማርገብ ካልቻሉ ደም መፋሰስ ከግዛቱ አልፎ ይስፋፋል የሚል ስጋት እንዳላቸውም የተናገሩት ኃላፊው፤ "የደቡብ ሱዳን መንግስት በሁከቱ ላይ ፈጣን፣ ጥልቅ እና ገለልተኛ ምርመራ ማካሄድ እና ተጠያቂ የሆኑትን ሁሉ በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ተጠያቂ ማድረግ አለበትም" ሲሉም አክለዋል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ኤጀንሲ (ዩኤንኤች ሲአር) ግጭቱ በነሐሴ ወር በላይኛው ናይል መንደር ውስጥ ከጀመረው ጦርነት የቀጠለ ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወደ ሌሎች የ የጆንግሌይ እና ወደ ሌላሎች ግዛቶችና አካባቢዎች መዛመቱ ገልጿል።

በግዛቱ የሚገኙ የሐይማኖት አባቶችም በተመሳሳይ በተቀናቃኝ ወጣቶች መካከል የተፈጠረው ግጭት ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ መምጣቱን በመግለጽ፣ ተፈናቃዮች ወዳሉባቸው መጠለያ ጣቢያዎችም ጭምር መዛመቱንም አመልክተዋል።



በደቡብ ሱዳን አንዳንድ አካባቢዎች በግጦሽ፣ በውሃ፣ በእርሻ መሬት እና በሌሎች ሀብቶች ምክንያት የሚነሱ ግጭቶች ብዙ ጊዜ ወደ ሞት የሚያደርሱ ሁከቶች እንደሚፈጥሩ ይታወቃል።

## አሜሪካ ዘመናዊ የአየር መቃወሚያ ዩክሬንን ልታስታጥቅ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጆ ባይደን አስተዳደር እጅግ ዘመናዊ ናቸው የሚባሉትን የአየር መቃወሚያዎች ለዩክሬን እንደሚልክ አስታወቀ።

‘ፓትሪዮት’ የሚል ስያሜ ያላቸው እነዚህ ውስብስብና የላቁ የአየር መቃወሚያዎች ለዩክሬን በዚህ ጊዜ ያስፈለጉት ሩሲያ በተከታታይ እየሰነዘረች ያለችውን የአየር ድብደባ ለመግታት ሲሆን ሩሲያ ከቅርብ ወራት ወዲህ በኢራን ሠራሽ 'ካሚካዚ' ድሮኖች እንዲሁም በተወንጫፊ ሚሳኤሎች እየሰነዘረች ባለችው ጥቃት ብዙ የዩክሬን ከተሞችን በጨለማ ከመዋጥ ለመታደግ ጭምር ነው።

ሩሲያ በተለይም በዚህ የውርጭ ወራት የኃይል አቅርቦትን የሚያሳልጡ መሠረተ ልማቶች ላይ ለይታ ድብደባ ማድረሷ የሚሊዮን ዩክሬናውያን ቤቶች ያለማሞቅያ አስቀርታቸዋለች። ባይደን ‘ፓትሪዮት’ የአየር መቃወሚያዎች ለዩክሬን እንደሚሰጡ በእነዚህ ሁለት ሦስት ቀናት ውስጥ በይፋ መግለጫ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል።



ዩክሬን ምዕራባውያን የላቁ የአየር መቃወሚያዎችን እንዲለግሷት ስትወተውት ቆይታለች።‘ፓትሪዮት’ የሚባለው ይህ መቃወሚያ አሜሪካ አለኝ ከምትላቸው እጅግ ዘመናዊ የአየር መቃወሚያዎች አንዱ ሲሆን ለዩክሬን የምትሰጠው ግን በተመጠነ መንገድ እንደሚሆን የጦር አዋቂዎች እየገለጹ ይገኛሉ።

ለዚሁ የአየር መቃወሚያ ሲባል ዩክሬናውያን ወታደሮች ጀርመን ግራፈንዎር በሚገኘው የአሜሪካ የጦር ሰፈር በአጠቃቀሙ ዙርያ ልዩ ስልጠና በድብቅ የሰጠች ሲሆን ሩሲያ ግን የፓትሪዮት ሲስተም ዩክሬን ከገባ በኋላ ዒላማዋን ለማድረግ ዝታለች።

የቢቢሲው የጦርነት ተንታኝ ጆናታን ቤል እንደሚለው ይህ የአሜሪካ እርምጃ የሚያሳየው አሁን ለዩክሬን ትልቁ ስጋት የሩሲያ የምድር ጦር ሳይሆን የአየር ኃይል መሆኑን ነው። የሩሲያ የድሮንና የሚሳኤል ጥቃቶች በዩክሬን የማይናቅ የኃይልና የውሃ አቅርቦት እጥረትና ምስቅልቅል ማስከተሉን ጆናታን ይገልጻል።

ቀደም ሲልም ዩክሬን በምሕጻር ናሳም የሚባሉትን እንዲሁም 'አይሪስ ቲ' የሚባሉ ዘመናዊ የአየር መቃወሚያዎችን ከምዕራባዊያን ያገኘች ሲሆን ይሁንና እነዚህ መቃወሚያዎች የሩሲያን የአየር ጥቃት ለማቆም በቂ ሆነው ስላልተገኙ ነው ‘ፓትሪዮት’ በአሜሪካ ለዩክሬን እየተለገሰ ያለው።

አሁን አሜሪካ ለዩክሬን ልትሰጥ ያሰበቻቸው ‘ፓትሪዮት’ የአየር መቃወሚያ አንዱ ባትሪ ብቻ እስከ ሦስት ሚሊዮን ዶላር እንደሚያወጣ ዋሺንግተን ፖስት በ2017 መዘገቡንም ቢቢሲ አውስቷል።

# ስፖርት



## በበጀት እጥረት ከአህጉራዊ ውድድር የተሰናበተው የካራቴ ብሄራዊ ቡድን

ብርሃን ፈይሳ

የደቡብ አፍሪካዋ ከተማ ደርባን 21ኛውን የመላው አፍሪካ ካራቴ ቻምፒዮና በቅርቡ አካሂዳለች። በዚህ ውድድር ከተካፈሉት አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ብትሆንም፤ ወደ ውድድሩ ያቀናው ብሄራዊ ቡድን በገንዘብ እጦት ምክንያት በጊዜ ከውድድር እንደተሰናበተ ገልጿል። ቡድኑ ከደርባን መመለሻ የሚሆነውንም ወጪ በከተማዋ በሚኖረው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ እንደተሸፈነለት ቅሬታውን አቅርቧል።

ቡድኑን ይዘው ወደ ደርባን የተጓዙት ኢንስትራክተር ኑሩ መሃመድ፤ በአራት ተወዳዳሪና በአንድ አሰልጣኝ የተወከለው ቡድን በውድድሩ ረጅም ርቀት መጓዝ የሚችል እንደነበረ ይናገራሉ። የቡድኑ አባላት የተመረጡት የኢትዮጵያ ለሁሉም ክፍት የሆነ የካራቴ ውድድር ሲሆን፤ በኬንያ ናይሮቢ በተካሄደ ውድድር አንድ የብር እና አራት የነሃስ ሜዳሊያዎችን አግኝቶ ነበር። ቡድኑ ለደቡብ አፍሪካው ውድድርም የ10 ቀናት ዝግጅት ካደረገ በኋላ ወደ ደርባን ማቅናቱን ያስታውሳሉ።




ብሔራዊ ቡድኑ በውድድሩ ወቅት የገንዘብ ችግር የገጠመው ቢሆንም በቡድን ውጤት ምርጥ ስድስት ውስጥ መግባት ችሎ ነበር። ወደ ደርባን ለሚያደርገው ጉዞው ትኬት እስከመቁረጥ በነበረው ሂደት የፋይናንስ ችግር ገጥሞት የነበረው ቡድን የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚዎች ከኪሳቸው ገንዘብ ወጪ በማድረግ ሲያግዙት ቆይተዋል። በጉዞው ዕለትም በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስር ዴኤታ የሸኘት መርሃ ግብር መዘጋጀቱ የቡድኑን የገንዘብ ችግር ይቀርፋል ተብሎ ቢታሰብም እንዳልተሳካ ተገልጿል። የቡድኑ አባላት ግን በውድድሩ ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው በማመናቸው ጉዞውን በራሳቸው ገንዘብ ለማድረግ እንደወሰኑ አሰልጣኙ ያብራራሉ።

በፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ በኩል የተለያዩ ጥረቶች በማድረግ ቡድኑ ወደ ደርባን ካቀና በኋላም ሂደቱን ጨርሶ ወደዚያው የመጓዝ አማራጭ ተይዞም ነበር። በዚህም ኅዳር 21/2015 ዓ.ም ወደዚያው የተጓዘው ቡድን ከጆሃንስበርግ ወደ ደርባን ያለውን ረጅም መንገድ በመኪና በመጓዝ፣ አነስተኛ ሆቴል ፈልጎ በማረፍ እንዲሁም ስልክና ፓስፖርት በእዳ አስይዞ ትጥቅ እስከመግዛት የደረሰ መሰዋዕትነትን ለመክፈል መገደዱን ጠቁመዋል። የቡድኑ አባላት በውድድሩ የገጠማቸውን ችግሮች ታግሰው እስከ አራት ዙሮች በፉክክር ቢጓዙም በውድድሩ ለመቆየት ተጨማሪ መመዝገቢያ መክፈል የነበረበትን ገንዘብ ባለማግኘቱ ምክንያት መሰናበቱ የግድ እንደሆነ ገልጸዋል። ቡድኑ በእዳ የተያዙትን ንብረቶች ለማስመለስ እና ወደአገር ቤት ለመመለስ ደግሞ ሌላ ወጪ በማስፈለጉ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን ከማስቸገር ውጭ አማራጭ አልነበረውም።

አገር በምትወከልበት በዚህ ውድድር ላይ ለመካፈል ፌዴሬሽኑ እንዲሁም ስራ አስፈጻሚው ብዙ ጥረቶችን አድርጓል። ነገር ግን ስፖርቶችን በበላይነት የሚመራው ሚኒስትር መስሪያ ቤት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ምክንያት በሰው አገር ላይ የቡድኑ አባላት መጉላላቱን ተናግረዋል። ያም ሆኖ የደርባን ከተማ ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን ጥረት ኅዳር 27/2015 ዓ.ም የቡድኑ አባላት ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለቡድኑ አቀባበል ቢያደርግላቸውም ችግሩ ለምን እንደተከሰተ እንዲሁም በስነልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ተወዳዳሪዎች ማብራሪያ የሚሰጥ አካል እንዳልነበረም አስረድተዋል። በመሆኑም በተመሳሳይ መንገድ በግለሰቦች ወጪ ስፖርተኞቹ ወደየመጡበት እንዲመለሱ መደረጉን አሰልጣኝ ኑሩ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ካራቴ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢትዮጵያ በዴቻ፤ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የፈረንጆቹ ዓመት የጃፓን መንግስት ዕውቅና ከሰጣቸው ተቋማት መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ካራቴ ፌዴሬሽን መሆኑን ይናገራሉ። በምስራቅ አፍሪካም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በስፖርቱ አምስት ሜዳሊያዎች የተመዘገበበት ዓመት መሆኑን በማስታወስ በደርባኑ ውድድር ላይም ውጤታማ ለመሆን ዝግጅት መደረጉን ያስረዳሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ድጎማ እጅግ አነስተኛ ከመሆኑም ባለፈ በዚህ ዓመት ምንም ዓይነት ገንዘብ ለፌዴሬሽኑ እንዳልተለቀቀ ይጠቁማሉ። የቡድኑ ዝግጅትም እሳቸውን ጨምሮ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከኪሳቸው ገንዘብ በማውጣት እንዲሁም ሆቴሎችን ትብብር በመጠየቅ ነበር የተከናወነው። ፌዴሬሽኑ ስፖርቱን ለሚመራው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስለውድድሩ አስታውቆ ድጋፍ እንደሚደረግለትም ቃል ተገብቶለት እንደነበር ያስታወሱት ፕሬዚዳንቱ፣ ይሁንና የጉዞው ወቅት ሲደርስ የተባለው ባለመሆኑ ፕሬዚዳንቱ በራሳቸው ገንዘብ የጉዞ ትኬት መቁረጣቸውን ጠቁመዋል። በቡድኑ አባላት ላይ የስነልቦና ጫና እንዳይደርስባቸው ስራ አስፈጻሚው የድጋፍ ሂደቱን በመቀጠል ወደ ደርባን ይዞ የመሄድ አማራጭ እንደያዘ የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፣ ነገር ግን ጥረቱ ስኬታማ ሊሆን እንዳልቻለ ያስረዳሉ። ቡድኑ ወደ አገር ከገባም በኋላ የተደረገላቸው ምንም ዓይነት ነገር የለም ሲሉም ወቀሳቸውን ያቀርባሉ።

በጉዳዩ ዙሪያ ማብራሪያ ተጠይቀው ምላሽ የሰጡት በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ፤ ፌዴሬሽኑ አስቀድሞ ክስ እንደነበረበት ያስታውሳሉ። ከብሄራዊ ቡድኑ ምርጫ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያቀረቡ አካላትን በማጣራት ላይ እንደነበሩ የገለጹት አቶ ተስፋዬ፣ ይሁንና በውድድሩ ተሳታፊ እንደሚሆኑ አሳውቀው መቅረታቸው አገርንም የሚያስቀጣ በመሆኑ የተጀመረው እንዲቀጥል እንደተነገረው ያስረዳሉ። ይሁንና ቡድኑ ሲመለስም ሪፖርት ማቅረብ ሲገባቸው እንዳላቀረቡ ተናግረዋል። ‹‹ከውድድሩ አስቀድሞም እቅዳቸውንና የውድድር ወቅቱን አላሳወቁም›› ያሉት አቶ ተስፋዬ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቡድኑ ከውድድር ሲመለስ ድጋፉን እንደሚያደርግ አሳውቆ ነበር ገልጸዋል። ‹‹አብዛኛዎቹ የስፖርት ማህበራት አስቀድሞ ከማሳወቅ ይልቅ በድንገት ቀርበው ድጋፍ ይጠይቃሉ። ይህ ደግሞ ከመንግስት የበጀት አሰራር ጋር ይጣረሳል›› የሚሉት አቶ ተስፋዬ፣ በቀጣይም በፌዴሬሽኑ የተጀመረውን አቤቱታ ለማየትና ጉዳዩም ላይ እልባት ለመስጠት ቀጠሮ መያዙን አስረድተዋል።


### ማስታወቂያ

“አማና የበጎ አድራጎት ድርጅት “የተባለ ቦርድ መር ድርጅት ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል ተቃዋሚ ካለ እስከ ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ።

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

### ማስታወቂያ

❖ “የኢትዮጵያ የሙያ ማህበራት ህብረት “የተባለ “ህብረት” ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል ተቃዋሚ ካለ እስከ ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ።

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

### ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 728 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0000056421 ጥሩ ቢዝነስ ግሩፕ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር ሲሆን የግዥ ደረሰኝ ውስጥ ቁጥር 00000204 ግዥ የፈፀምንበት ደረሰኝ ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ።

**የግብር ከፋይ ስም ጥሩ ቢዝነስ ግሩፕ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም መሰሉ ግርማ ወንድምአገኘሁ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-07303 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር RM26CF17.675232786 ሞዴል RM26 የሞተር ቁጥር Traller የሊብሬ ቁጥር 0278549 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/4/2015ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

### የጨረታ ማስታወቂያ

የትምህርት ሚኒስቴር በ2015 በጀት አመት በኤሌክትሮኒክ የመንግሰት ግዥ ሥርዓት (Electronic Government Procurement system) በመጠቀም በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ ለመፈጸም ይፈልጋል።

በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ የመንግሰት ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ www.egp.ppa.gov.et ላይ በመመዝገብ ለዚሁ ጨረታ የተዘጋጀውን የጨረታ ማስታወቂያ የማግኘት እና ጨረታውን በሲስተሙ መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እየገለጽን፣ ተጫራቾች ማሟላት የሚጠበቅባቸው ዝርዝር የህጋዊነት ሰነዶች በሲስተሙ ላይ ይፋ በተደረገው የጨረታ ማስታወቂያ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡ የጨረታ ማስታወቂያው በሲስተሙ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ለ 20 ተከታታ ቀናት ለተጫራቾች ክፍት ስለሚሆን ተጫራቾች በሲስተሙ በመመዝገብና የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን

| ተ.ቁ | የእቃው ዓይነት | የግዥ መለያ ቁጥር | ጨረታው የሚከፈትበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|
| 1 | Procurement of uniform cloth | MoE-NCB-G-0002-2015-BID | ታህሳስ 27 ቀን 2015 ሰዓት 4፡30 |
| 2 | Procurement of Tyre, Battery & Protection Equipment for vehicles | MoE-NCB-G-0004-2015-BID | ታህሳስ 25 ቀን 2015 ሰዓት 4፡30 |
| 3 | Procurement of sanitary materials | MoE-NCB-G-0001-2015-BID | ታህሳስ 26 ቀን 2015 ሰዓት 4፡30 |

ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚከናወን የጨረታ አከፋፈት ሂደት ላይ መሳተፍ የሚችሉ ሲሆን፣ ባለስልጣኑ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ተጫራቾች ከሲስተሙ በተጨማሪ ማብራሪያ ሲፈልጉ ከዚህ በታች በተጠቀሰው የስልክ አድራሻ በመደወል መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

ስልክ +251 111400312

**የትምህርት ሚኒስቴር**